መቀመጧ ቅዱስ ዮሐንስ ሐዋርያ በዕለተ ዓርብ ከእግረ መስቀል በአደራ ከተቀበላት በኋላ በቤተ ዮሐንስ ከመቀመጧ ጋር በምሥጢር ይገናዘባል:: በዚህም የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም ሊቃውንት ከላይ በዝርዝር ያስቀመጡትንና ኃያሉ አምላክ እናቱ ድንግል ማርያም ለዮሴፍ እንድትታጭ ያደረገበትን ረቂቅ ጥበብና ድንቅ ምሥጢር ይገነዘቧል::

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ከላይ የተመለከትነውና እመቤታችን ድንግል ማርያም ለአረጋዊው ጻድቅ ለቅዱስ ዮሴፍ እንድትታጭ (በአደራ እንድትሰጥ) ያስፈለገበት ዋነኛው ዓላማ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ ልደት መፈጸሙን በመግለጥና በማረጋገጥ ቅዱስ ወንጌል "... ተነሣ፥ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ ..." (ማቴ. 2፥13-20) ሲል መልአከ እግዚአብሔር ለቅዱስ ዮሴፍ አረጋዊ ገልጾ በተናገረው አማናዊ የምስክርነት ቃል አጽንቷል፣ አትሟል፣ ደምድሟል:: በዚህም ማስረጃነት ወንጌላውያን ዮሴፍን የድንግል ማርያም እጮኛ እያሉ የገለጹት እስከ ልደተ ክርስቶስ ድረስ ብቻ መሆኑን፤ ከዚያ በኋላ ግን መልአከ እግዚአብሔርም ሆነ ወንጌላውያን "... ሕፃኑንና እናቱን፣ ዮሴፍንም ..." (ማቴ. 2፥11፣ 13-14፤ 20-21፤ ሉቃ. 2፥16) በማለት ጠንቅቀው መናገራቸውንና መመስከራቸውን ልብ ይሏል::(263)

## 4.1.6.2 የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም

ሔልቪዲየስ ያቀረበው ሌላው አስተሳሰብ ደግሞ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት "የጌታ ወንድሞች" የሚሉትን ገጸ ንባባት መነሻ ያደረገ

(263) Stanley Samuel Harakas, *Exploring Orthodox Christianity: Orthodox Christian Belief About the Bible: Real Answers to Real Questions from Real People* (Minneapolis, Minnesota: Light & Life Publishing Company, 2003), 115, 118. Pope Shenouda III, *The Perpetual Virginity of the Virgin St. Mary*, 5-6. Pope Shenouda III, *Comparative Theology*, 177.



ነው:: ሔልቪዲየስ ለዚህ አባባሉ በቀዳሚነት የጠቀሰው ዋነኛው የቅዱስ መጽሐፍ ክፍለ ንባብ "ወኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ ወለደት ወልዳ ዘበኵሩ፤ የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም" (ማቴ. 1፥25) የሚለውን ነበር:: ከዚህ ገጸ ንባብ በመነሣትም አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የበኵር ልጇ የተባለውን መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ ከወለደች በኋላ የግድ በግብር አውቋታል በማለት ያስተምር ነበር:: ሔልቪዲየስ በዚህ የተሳሳተ ትምህርቱ አረጋዊው ቅዱስ ዮሴፍ በትዳር አብራው ከነበረችውና በሞት ከተለየችው ሚስቱ አስቀድሞ የወለዳቸውንና ወንጌላውያን "የጌታ ወንድሞች" እያሉ የሚጠሯውን ልጆቹን የእመቤታችን ልጆች እንደሆኑ አድርጎም ተናግሮአል::(264)

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ለዚህ ሔልቪዲየሳዊ ክሕደት ምላሽ በሰጡበት የምሥጢር መድበላቸው "ማወቅ" የሚለውን ቃል በሁለት ዐበይት መንገዶች ተርጉመውታል:: ይኸውም "ማወቅ" የሚለው ቃል በመጀመሪያ ትርጓሜው ግንዛቤንና መረዳትን ወይም ማስተዋልን የሚገልጽ ሲሆን፤ በሁለተኛው ትርጓሜ ደግሞ የግብር ዕውቀ ትን (ሩካቤን) ያመለክታል:: ለዚህም "አዳምም ሚስቱን ሔዋንን አወቀ፤ ፀነሰችም ቃየንንም ወለደች:: ... ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደች" (ዘፍ. 4፥1-2)፤ "... ሕልቃናም ሚስቱን ሐናን አወቃት፤ እግዚአብሔርም አሰባት፤ የመፀነስዋም ወራት ካለፈ በኋላ ሐና ወንድ ልጅ ወለደች" (1ኛ ሳሙ. 1፥19-20) የሚሉት ቃላተ መጻሕፍት በቂ ማስረጃዎችና ምስክሮችም ናቸው::

እንደ ሔልቪዲየስ አመለካከት ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም የበኵር ልጇ የተባለውን ኢየሱስ ክርስቶስን እስክትወልደው ድረስ ጠባቂዋ የሆነው ቅዱስ ዮሴፍ በግብር ዕውቀት ማለትም አዳም ሚስቱ

(264) St. Jerome, "The Perpetual Virginity of Blessed Mary," 339-343. Pope Shenouda III, *Comparative Theology*, 179. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 8. Pope Shenouda III, *The Perpetual Virginity of the Virgin St. Mary*, 7.

ሔዋንን፣ ሕልቃና ደግሞ ሚስቱ ሐናን ባወቀበት ግብር አላወቃትም ነበር:: ይሁን እንጂ እመቤታችን የበኵር ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን ከወለደች በኋላ ግን ምስጋና ይግባትና አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ አዳም ሔዋንን፣ ሕልቃና ሐናን ባወቀበት ግብር አውቋታል በማለት በማቴዎስ 13÷53-55 ላይ «... ይህን ጥበብና ተአምራት ይህ ከወዴት አገኘው? ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን? እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ተሰናከሉበትም» ተብሎ ከተጻፈውና አይሁድ ከተሰናከሉበት የክሕደት ቃል ጋር በማጣመር እነዚህ የጌታ ወንድሞቹና እኅቶቹ የተ ባሉት ከእመቤታችንና ከአረጋዊው ዮሴፍ የተወለዱ ናቸው ብሏል:: በዚህ አስተሳሰቡም ሔልቪዲየስ «እስከ» የሚለውንና ወንጌላዊው የገለጸውን የጊዜ ገላጭ ቃል ፍጻሜ፣ የተወሰነና አጭር የሆነ ገደብ ሰጥቶ ተርጉሞታል::(265) ይህ ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ የወጣና ፈጽሞ ስሕተት በመሆኑ ትክክለኛ ፍቺውንና ቀጥተኛ ትርጓሜ ምሥጢሩን ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን::

### 4.1.6.2.1 «በኵር» የሚለው ቃል ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ፤

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንገነዘበው በኵር የሚለው ቃል ትርጉም ከሰውም ሆነ ከእንስሳ ለመጀመሪያ ጊዜ የእናቱን ማኅፀን ከፍቶ የሚወጣ ማለት ነው እንጂ የግድ ሌላ ተከታይ ያለው ማለት አይደለም:: ለዚህም «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው:- በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም ማኅፀንን የሚከፍት በኵር ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ የእኔ ነው» (ዘጸ. 13÷1-2) ተብሎ የተጻፈው ቃለ መጽሐፍ በቂ ማስረጃና ምስክር ነው::

(265) Rene' Laurentin, *The Hail Mary: Its Meaning and Its Origin* (Milford, Ohio: Faith Publishing Company, 1991), 23. እንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፤ *ክብረ ድንግል*፣ ገጽ 2:: St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 9.



ከዚህም ሌላ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን በበግዐ ፋሲካው (በፋሲካው በግ) ደም አማካይነት ከአባር፣ ከቸነፈር እንዲሁም ከሞተ በኵር በታደገባትና ከግብፅ ባርነት ነጻ ባወጣባት ዕለት ሊቀ ነቢያት ሙሴንና ካህኑ አሮንን «በዚያች ሌሊት በግብፅ አገር አልፋለሁ፣ በግብፅም አገር ከሰው እስከ እንስሳት ድረስ በኵርን ሁሉ እገድላለሁ» (ዘጸ. 12÷12) ሲል ተናግሮአል:: ይህ ማለት ከላይ በገለጥነው ትርጓሜ መሠረት አምላከ እስራኤል እግዚአብሔር በሞተ በኵር የመታቸውና የቀጣቸው ከሰውም ሆነ ከእንስሳት ወገን ማኅፀንን ከፍተው የወጡትን በኵራት ሁሉ እንጂ የግድ ተከታይ ያላቸውን ብቻ ለይቶ አይደለም:: ምክንያቱም ከላይ እንዳየነው በኵር የሚለው ቃል የሚያመለክተው ለመጀመሪያ ጊዜ የእናት ማኅፀን ከፋች የሆነውን ማለት ብቻ እንጂ ተከታይ መኖሩና አለመኖሩ ከቃሉ መሠረታዊ ፍቺና ምሥጢር ጋር ግንኙነት የለውም::

ስለሆነም ሊቀ ነቢያት ሙሴ ይህንን ቀጥተኛና አማናዊ ትርጓሜ በመግለጥ የፀአተ እሥራኤልን (የእሥራኤላውያንን ከግብፅ መውጣት) ታሪክ በተናገረበት መጽሐፉ:- «እንዲህም ሆነ፤ እኩለ ሌሊት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር÷ በዙፋኑ ከተቀመጠው ከፈርዖን በኵር ጀምሮ በግዞት እስካሉት እስከ ምርኮኞቹ በኵር ድረስ÷ የግብፃውያንን በግብፅ ምድር የተገኘውን በኵር ሁሉ÷ የእንስሳውንም በኵሮች ሁሉ መታ::» (ዘጸ. 12÷29) ሲል መስክሮአል:: በዚህ ገጸ ንባብ መሠረት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ግብፃውያንን በሞተ በኵር በመታቸው ጊዜ ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ፤ ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ ያሉትንና ለመጀመሪያ ጊዜ ማኅፀን የከፈቱትን በሙሉ አስተካክሎና አንድ አድርጎ እንደገደለ እንጂ ተከታይ ያላቸውን ብቻ ለይቶ እንዳልገደለ ይገነዘቧል::(266)

(266) Pope Shenouda III, *Comparative Theology,* 172-174. St. Jerome, "The Perpetual Virginity of Blessed Mary," 339. እንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፤ *ክብረ ድንግል*፣ ገጽ 2-3:: Pope Shenouda I II, *The Perpetual Virginity of the Virgin St. Mary,* 2-3. St. Jerome,, *St. Mary the Ever Virgin,* 14-15.

ይሁን እንጂ ሔልቪዲየስ ይህንን ቀጥተኛና ትክክለኛ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ ካለመረዳቱና ምሥጢሩንም ካለመጠንቀቁ የተነሣ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ «... በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ÷ የበኩር ልጅዋንም ወለደች» (ሉቃ. 2÷7) ብሎ የተናገረውን ኃይለ ቃል ከላይ አርእስቱን፣ ከታች ኅዳጉን ሳይመለከትና ሳያገናዝብ በማውጣት በኩር የሚለው መጠሪያ ስያሜ የግድ ሌላ ተከታይ ወንድሞችና እኅቶች ሳሉት ብቻ የሚያገለግል በመሆኑ ወንጌላዊው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን «በኩር» ማለቱ ሌሎች ወንድሞችና እኅቶች እንዳሉት ያስረዳል ብሏል::(267)

ለዚህ የተሳሳተ አመለካከቱም ከዚህ የሚከተሉትን ገጸ ንባባት ይጠቅሳል:: «ገናም ለሕዝቡ ሲናገር÷ እነሆ÷ እናቱና ወንድሞቹ ሊነጋ ገሩት ፈልገው በውጭ ቆመው ነበር» (ማቴ. 12÷46)፤ «ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕ ቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን? እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ተሰና ከሉበትም:: ... በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም» (ማቴ. 13÷55-58፤ ማር. 6÷3)፤ «ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ» (ዮሐ. 2÷12፤ 7÷3-5)፤ «... እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር» (የሐዋ. ሥራ 1÷14)፤ «እንደ ሌሎቹ ሐዋርያትና እንደ ጌታ ወንድሞች ...» (1ኛ ቆሮ. 9÷5)፤ «ነገር ግን ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በቀር ከሐዋርያት ሌላ አላየሁም» (ገላ. 1÷19)(268)

(267) McHugh, *The Mother of Jesus in the New Testament*, 200-254.

(268) St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 12. Pope Shenouda III, *Comparative Theology*, 182-183: እንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፤ *ክብረ ድንግል*፣ ገጽ 2-3:: Pope Shenouda III, *The Perpetual Virginity of the Virgin St. Mary*, 10.



በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም አስተምህሮ መሠረት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና የትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) ዐቢይ ክፍለ ትምህርት ነው:: ይህንንም ታላቅ የሥጋዌ ምሥጢር የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም ሊቃውንት «አንድያ (ብቸኛ) ልጅ የሆነ ሁሉ የበኩር ልጅ ነው፤ የበኩር ልጅ የሆነ ሁሉ ግን የግድ አንድያ (ብቸኛ) ልጅ አይደለም»(269) በማለት ከላይ በገለጥነውና በዘጸአት 13÷2፤ 12÷29 ላይ በተጠቀሱት ቃላተ መጻሕፍት ማስረጃነት በሚገባ ገልጸውታል:: በዚህ መነሻነት ቀጣዩ ሔልቪዲየሳዊ ጥያቄ ደግሞ ስለምን ወንጌላዊው «የበኩር ልጇን ወለደች» (ሉቃ. 2÷7) ሲል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የድንግል ማርያም የበኩር ልጅ ብሎ ጠራው? የሚል ነው::

የቤተ ክርስቲያን መተርጉማን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በኩር» ተብሎ የተጠራበት ዋነኛው ምክንያት የድንግል ማርያም ብቸኛ ልጅ ማለትም ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጇ መሆኑን ለመግለጥ እንደሆነ በሚገባ አስረድተዋል:: ከዚህም ሌላ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኩር መባሉ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውንና በኵረ ኵሉ ፍጥረት የሆነውን የእግዚአብሔር አብን የባሕርይ ልጅ በሥጋ መውለዷንና በዚህም እሙ ስምዓክ፣ ጠባዴተ ስምዓክ መሆኗን ለመግለጥም ነው::(270)

መጻሕፍት አምላካውያት በመተባበር መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን በኩር በማለት ይጠሩታል:: ለዚህም «እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት÷ በሰማይና በምድር

(269) Harakas, *Exploring Orthodox Christianity: Orthodox Christian Belief About the Bible: Real Answers to Real Questions from Real People*, 138. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 14, 56. St. Cyril the Great, *He Became Flesh*, trans. Matthias F. Wahba (San Francisco: St. Antonius Publishing Center, 1992), 14-15. እንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፤ *ክብረ ድንግል*፣ ገጽ 2::

(270) እንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፤ *ክብረ ድንግል*፣ ገጽ 2::

ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና፤ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው:: ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው» (ቈላ. 1÷15-17)፤ «ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ» (መዝ. 109÷3)፤ «ከመላእክትስ:- አንተ ልጄ ነህ÷ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ÷ ደግሞም:- እኔ አባት እሆነዋለሁ÷ እርሱም ልጅ ይሆነኛል ያለው ከቶ ለማን ነው? ደግሞም በኵርን ወደ ዓለም ሲያገባ:- የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ለእርሱ ይስገዱ ይላል» (ዕብ. 1÷5-6፤ መዝ. 2÷7) የሚሉት ቃላተ መጻሕፍት በቂ ማስረጃዎች ናቸው:: በመሆኑም በእነዚህ ገጸ ንባባት ማስረጃነት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት በተወለደው ቀዳማዊ ልደቱ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የእግዚአብሔር አብ የበኵር ልጅ መሆኑን ይገነዘቧል::

እንግዲህ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ እንደ ሔልቪዲየስ አባባል በኵር የሚለው ስያሜ የግድ ተከታይ ያስፈልገዋል ከተባለ እግዚአብሔ ር አብ ከባሕርይ ልጁ ከእግዚአብሔር ወልድ ሌላ ልጅ አለው ማለት ነውን? ይህማ እንዳይባል ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም:: በአባቱ እቅፍ ያለ አንድያ ልጁ እርሱ ተረከው እንጂ» (ዮሐ. 1÷18)፤ ዳግመኛም «... እግዚ. አብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዶአልና» (ዮሐ. 3÷16) በማለት የእግዚአብሔር አብ የበኵር ልጅ ተ ብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጠራውና የተመሰከረለት አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የአብ አንድያ ልጁ መሆኑን በግልጽ አስረድቷል:: (ማቴ. 3÷17፤ 16÷16፤ 17÷5፤ 1ኛ ጴ ጥ. 1÷16-18)[271] በዚህም መሠረት ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከባሕርይ አባቱ ከአብ ያለ እናት በተወ ለደው ቀዳማዊ ልደቱ የእግዚአብሔር አብ የበኵር ልጅ ሲሆን፤

[271] *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 71:: Hainsworth, "The Ever-Virginity of the Mother of God," 3, St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin,* 14-15. St. Jerome, "The Perpetual Virginity of Blessed Mary," 339-340. እንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ *ክብ ረ ድንግል፣* ገጽ 2-3::



ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው ደኃራዊ ልደቱ ደግሞ የድንግል ማርያም የበኵር ልጅ መሆኑን ልብ ይሏል::

## 4.1.6.2.2 «እስከ» የሚለው ቃል ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ፤

ኦርቶዶክሳውያን መተርጉማን እንደገለጹት «እስከ» የሚለው የጊዜ ገላጭ ቃል [Adverbial Time Indicator] በሁለት ዓይነት መንገድ ይፈታል፣ ይተረጎማል:: ይኸውም በቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት እንደተጻፈው «እስከ» የሚለው ቃል ፍጻሜ (ወሰን፣ ገደብ) ባለው፤ እንዲሁም ፍጻሜ (ወሰን፣ ገደብ) በሌለው ነገር እየገባ የሚተረጎም ቃል ነው:: በዚህ መሠረት በወንጌለ ቅዱስ ማቴዎስ 1÷25 ላይ «የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም» ተብሎ በተጻፈው ገጸ ንባብ ውስጥ «እስከ» የሚለው ቃል ትርጓሜ ምሥጢሩ ፍጻሜ የሌለው «እስከ» ነው:: ይህንንም ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አያሌ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃነትና ምስክርነት በሚገባ መረዳትና መገንዘብ ይቻ ላል::[272]

- በኦሪት ዘፍጥረት 8÷7 ላይ:- «... ቁራውም የጥፋት ውኃ <u>እስኪጎድል ድረስ</u> አልተመለሰም» ተብሎ ተጽፏል:: ይህ ማለት ግን ኖኅ የጥፋት ውኃ መጉደሉንና መድረቁን ለማወቅ የላከው ቁራ የጥፋት ውኃ ከጎደለ በኋላ ወደ መርከቢቱ ተመለሰ ማለት አይደለም:: ይልቁንም ፈጽሞ ሳይመለስ ቀረ ማለት እንጂ::
- በኦሪት ዘፍጥረት 28÷15 ላይ:- «እነሆም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፣

[272] G ambero, *Mary and the Fathers of the Church: The Blessed Virgin Mary in Patristic Thought,* 171-177. Bauer. *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers,* 46. Pope Shenouda III, *Comparative Theology,* 179. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin,* 10 - 11. Pope Shenouda III, *The Perpetual Virginity of the Virgin St. Mary,* 7. እንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ *ክብረ ድንግል፣* ገጽ 3:: *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 207::

በምትሄድባትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፣ ወደዚህችም ምድር እመልስሃለሁ፤ የነገርኩህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና» ሲል ልዑል ባሕርይ እግዚአብሔር ለወዳጁ ለቅዱስ ያዕቆብ ነግሮታል:: የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ማለቱ ግን ለቅዱስ ያዕቆብ የሰጠውን ተስፋና የገባለትን ቃል ከፈጸመለት በኋላ የሚተወውና የሚረሳው ሆኖ አይደለም:: ይልቁንም ከዚያም በኋላ እስከ መጨረሻው ድረስ በረድኤት የማይለየውና የሚጠብቀው መሆኑን ያስረዳል፣ ያስገነዝባል::

❖ በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 6÷23 ላይ:- «የሳኦል ልጅ ሜልኮል እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም» ይላል:: እንደ ሔልቪዲየስና ተከ ታዮቹ አባባል በማቴዎስ 1÷25 ላይ የተጠቀሰውና «እስከ» የሚለው ቃል ፍጻሜ ያለው ነው ከተባለ ሜልኮል ከተሞች በኋላ ልጅ ወለደች ማለት ነውን? ስለዚህ ሔልቪዲየሳውያን «ሜልኮል እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም» ማለት ትርጓሜ ምሥጢሩ ከሞተችም በኋላ ፈጽማ ሳትወልድ ቀረች ማለት መሆኑን ሲረዱና ሲገነዘቡ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ሰው ዐረፍተ ዘመኑ በሞት ከተገታ በኋላ በመቃብር ውስጥ ሳለ መውለድ ፈጽሞ እንደማይችል ለሁሉ የታወቀና የተረጋገጠ እውነታ ነውና:: ስለሆነም ከዚህ ገጸ ንባብ «እስከ» የሚለው ቃል ፍጻሜ የሌለው መሆኑን ማስተዋል ይገባል::

❖ በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15÷35 ላይ «ሳሙኤልም እስከ ሞተበት ቀን ድረስ ሳኦልን ለማየት ዳግመኛ አልሔደም» ተብሎ ተጽፏል:: በአጭሩ ይህ ማለት ነቢየ እግዚአብሔር ሳሙኤል ከሞተ በኋላ ንጉሡ ሳኦልን በግድ አይቶታል አያሰኝም:: ይልቁንም ከዕለተ ሞቱም በኋላ ፈጽሞ አላየውም ማለት እንጂ:: በዚህም «እስከ» የሚለው የጊዜ ገላጭ ቃል ፍጻሜና



ወሰን የሌለው መሆኑን ይገነዘቧል::

❖ በትንቢተ ኢሳይያስ 22÷14 ላይ:- «ይህም ነገር በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ጆሮ ተሰማ:- እስክትሞቱ ድረስ ይህ በደል በእውነት አይሰረይላችሁም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር» የሚል ገጸ ንባብ እናገኛለን:: ታዲያ ሔልቪዲየስና ተከታዮቹ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአትና በደል በሕይወተ ሥጋ ሳሉ በንስሐ ተጸጽተው ወደ እርሱ ሳይለመለሱ ከሞቱ በኋላ እንዲሁ ይቅር ይላቸዋል ይሉ ይሆን? ይህ የተሠመረበት ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢሩ ኃጢአታችሁና በደላችሁ ከሞታችሁም በኋላ ፈጽሞ አይሰረይላችሁም ማለት ነው:: ምክንያቱም መጽሐፍ «እምድኅረ ሞቱ ለሰብእ አልቦቱ ንስሐ፤ ሰው ከሞተ በኋላ ንስሐ የለውም» ይላልና::

❖ በመዝሙር 122÷2 ላይ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት:- «እነሆ÷ የባሪያዎች ዓይኖች ወደ ጌታቸው እጅ እንደሆኑ÷ የባሪያይቱም ዓይን ወደ እመቤትዋ እጅ እንደሆነ÷ እንዲሁ እስኪምረን ድረስ ዓይ ናችን ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ነው» በማለት ተናግ ሮአል:: ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት እንዲህ ማለቱ እርሱም ሆነ ሕዝቡ ባሕረ ምሕረት ወደብረ ትዕግሥት የሆነውን የእግዚአብሔርን ምሕረትና ቸርነት ካገኙ በኋላ ዓይናቸውን ወደ ሰማይ አምላክ ከማንሣት ይከለከላሉ ማለት አይደለም::

ከላይ በዝርዝር ከተመለከትናቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ማስረጃዎች በተጨማሪ ከአዲስ ኪዳንም የሚከተሉትን ገጸ ንባባት ለአብነት ያህል እንጠቅሳለን::

❖ በማቴዎስ 22÷41-45 ላይ:- «ፈሪሳውያንም ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ:- ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው? ብሎ ጠየቃቸው:: የዳዊት ልጅ ነው አሉት:: እርሱም:-

እንኪያስ ዳዊት፦ ጌታ ጌታዬን፦ <u>ጠላቶችህን የእግር መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ</u> አለው ሲል እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል? ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው እንዴት ልጁ ይሆናል? አላቸው» ሲል ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እርሱ ማንነት ከፈሪሳውያን ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ ተናግሮአል። በዚህም ገጸ ንባብ መድኃኒታችን ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት በመዝ. 109፥1 ላይ የተናገረውን ቃለ ትንቢት ጠቅሶ በቀዳማዊ ልደቱ ስምባከ ዳዊት (የዳዊት አምላክ)፣ በደኃራዊ ልደቱ ደግሞ ወልደ ዳዊት (የዳዊት ልጅ) የመሆኑን ምሥጢር ገልጾ አስተምሮአል።

የሥነ መለኮት ምሁራን እንደሚያብራሩት ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት የእስራኤል ዘሥጋ ጠላት የነበረው ጎልያድን በአምስት ድንጋዮች አማካይነት ድል ማድረጉ (1ኛ ሳሙ. 17፥40)፤ በኋለኛው ዘመን አምላከ ዳዊት፣ ወልደ ዳዊት የተባለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የእስራኤል ዘነፍስ ጥንተ ጠላት የነበረውን ዲያብሎስን በአምስቱ ቅንዋተ መስቀል (ሳዶር፣ አላዶር፣ ዳናት፣ አዴራ፣ ሮዳስ) ድል ለመንሳቱ ምሳሌ ነው። በመሆኑም ከላይ የተሠመረበት ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠላቶቹ ተ ብለው የተገለጹትን ሞትንና ዲያብሎስን ማኅየዊ በሚሆን ሞቱና ትንሣኤው ድል ካደረገ በኋላ በሰማይ ደመና፣ በመላእክት ምስጋና፤ በብርሃን፣ በቅዳሴ፣ በሥልጣን ወደ ቀደመ ክብሩ እንደሚያርግና በባሕርይ አባቱ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ (በምልዓት፣ በጌትነትት አብን መስሎና ተካክሎ በዕሪና ክብር) እንደሚቀመጥ የሚያስረዳና የሚያስገነዝብ ነው። በአንጻሩ ደግሞ እንደ ሔልቪዲየስ አስተሳሰብ "እስከ" የሚለው ቃል ፍጻሜ ያለው ብቻ ከሆነ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ጠላቶቹ የተሰኙትን ሞትንና ዲያብሎስን ድል ካደረገ በኋላ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ (ዕሪና ክብር) አልተቀመጠም ማለት ይሆናል።



ይህ ደግሞ መጻሕፍት አምላካውያት "ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ" (ማር. 16፥19)፤ "መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ" (የሐዋ. ሥራ 7፥55-56) በማለት መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ዓለምን የማዳን ሥራውን ፈጽሞ በክብር ወደ ሰማይ ማረጉን፣ ወደቀደመ ክብሩ መመለሱንና በአብ ዕሪና (ፍጹም የጌትነት ክብር) መቀመጡን አስመልክቶ የሰጡትን አማናዊ ምስክርነት ማስተሐቀርና ማሳበል ነው። (መዝ. 46፥5፤ ሉቃ. 24፥50፤ ዮሐ. 3፥13፤ 7፥33-34፤ የሐዋ. ሥራ 1፥9-11፤ 1ኛ ጢሞ. 3፥16)

ሌላው ደግሞ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነቱን ሥራ ፈጽሞ በመላእክት ምስጋና፣ በሰማይ ደመና በክብር ከማረጉ በፊት ለቅዱሳን ሐዋርያት አምላካዊ አደራውን ሲያስተላልፍላቸው "... <u>እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ</u>" (ማቴ. 28፥20) ሲል የማይታጠፍ ተስፋ ሰጥቷቸዋል። ጌታችን ይህንን ማለቱ ግን ከዓለም ፍጻሜ በኋላ ከቅዱሳን ሐዋርያት የሚለይ ሆኖ አይደለም። ይልቁንም ከፍጻሜ ዘመን በኋላም እስከ ዘለዓለም ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ ማለቱ እንጂ።

ይህንን አስመልክቶ ራሱ ባለቤቱ በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር "ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጀሁላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ" (ዮሐ. 14፥2-3) ብሏል። ዳግመኛም ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "... እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን" (1ኛ ተሰሎ. 4፥17፤ ፊል. 1፥23፤ ዕብ. 13፥8፤ ራእ. 1፥17-18) በማለት ገልጾ መስክሮአል።

እንግዲህ ከላይ የጠቀስናቸውና በዝርዝር የተመለከትናቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ኃይለ ቃላት "እስከ" የሚለው የጊዜ ገላጭ ቃል

ፍጻሜ በሌለው ፍቺ የሚገለጽና የሚተረጎም መሆኑን በግልጽ ያስረዳሉ፣ ያስገነዝባሉ፡፡ በዚህም መሠረት ሔልቪዲየሳውያን የቅዱሳት መጻሕፍትን ገጸ ንባብና ትርጓሜ ምሥጢር ጠንቅቀው ካለማወቃቸውና ካለመረዳታቸው የተነሣ የተሰናከሉበትና በክሕደት አዘቅት ውስጥ የወደቁበት «የበኲር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም» የሚለው የማቴዎስ 1÷25 ገጸ ንባብ አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድያ ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን ከወለደችም በኋላ አዳም ሔዋንን፣ ሕልቃና ሐናን ባወቀበት ግብር ፈጽሞ አላወቃትም ተብሎ የሚተረጎም መሆኑን ይገነዘቧል፡፡

ቀደም ብለን በክፍል 4.1.6.2 ላይ እንደገለጥነው ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ለሔልቪዲየሳዊ የክሕደት ትምህርት በሰጡት ምላሻቸው «ማወቅ» የሚለውን ቃል በሁለት ዓይነት ፍቺ ተርጉመው ማስተማራቸውን ተመልክተናል፡፡ በዚህ መሠረት እስካሁን ድረስ «ማወቅ» የሚለው ቃል የግብር ዕውቀትን (ሩካቤን) ወክሎ የሚነገር መሆኑን ከቅዱሳት መጻሕፍት አይተናል፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ «ማወቅ» የሚለው ቃል ግንዛቤንና መረዳትን እንዲሁም ማስተዋልን የሚገልጽ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ በዚህ የትርጓሜ መንገድና ስልት መሠረት «የበኲር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም» የሚለው የማቴዎስ 1÷25 ገጸ ንባብ አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ እመቤታችን ድንግል ማርያም በአማን እሙ ለአምላክ፣ ወላዲተ አምላክ፣ ወላዲተ ቃል መሆኗን፤ ከእርሷ የተወለደው መሲሕ ክርስቶስም አምላክ፣ ወልደ አምላክ መሆኑን በዕለተ ልደት የተገለጠውን ሰማያዊ ምሥጢር አይቶ እስኪረዳ ድረስ አላወቀም፣ አልተረዳም፣ አልተገነዘበም፣ አላስተዋለም ማለት ነው፡፡

በዚና አበው ሊቃውንት ዘንድ [Patristic Scholars] የሰባክያን አክሊል፣ የአትሮንስ ንጉሥ" በመባል የሚታወቀው ስመ ጥሩው የቤተ



ክርስቲያን አባት ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዘመኑ ለነበረው ለንጉሡ አርቃድዮስ ከላይ የገለጥነውንና «የበኲር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም» የሚለውን የወንጌላዊውን ኃይለ ቃል በተረጐመበት ድርሳኑ አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኤፍራታ ቤተ ልሔም በተወለደባት ዕለት የተገለጡትን አምስት መሠረታዊ ነገሮች አይቶ እስኪረዳ ድረስ ድንግል የተባለች እርሷ (እመቤታችን ድንግል ማርያም)፣ ወልድ የተባለ ደግሞ እርሱ (መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) መሆኑን አላወቀም፣ አልተረዳም፣ አላስተዋለም ሲል ተናግሮአል፡፡

ዳግመኛም ሊቁ ኤራቅሊስ በሃይማኖተ አበው ይህንን ትርጓሜ በማጽናት አብራርቶና አፍታቶ ተናግሮአል፡፡ ሊቃውንቱ እንደገለጹት እነዚህ አምስት መሠረታዊ ነገሮች የተባሉትም፡- ምጽአተ ሰብአ ሰገል ዘምሥራቅ አምኃ (የጥበብ ሰዎች ከእጅ መንሻ ጋር ከሩቅ አገር መምጣት)፤ ሑረተ ኮከብ በካልእ ፍና (የብርሃናዊው ኮከብ በሌላ መንገድ /ከሰማይ ዝቅ፣ ከመሬት ብቅ ብሎ/ ወደ ኤፍራታ ቤተ ልሔም እየመራ መሔድ)፤ ሥርቀተ ስብሐተ እግዚእ ዐቢይ (ታላቁ የጌታ ክብር መታየት)፤ ቅዳሴ መላእክት (የቅዱሳን መላእክት ሰማያዊ ምስጋና)፤ ፍርሃተ ኖሎት (የእረኞች ፍርሃት)[273] ናቸው፡፡

አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ ድንግል ማርያም በቅዱሳት መጻሕፍት በኲር ተብሎ የተጠራውን አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድን እስክትወልድ፣ ሰብአ ሰገልም ለባሕርይ ጌትነቱ የሚገባውን አምኃ አምጥተው፣ በፊቱ ወድቀው ሲሰግዱለት አይቶ እስኪረዳ ድረስ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ መሆኗን፣ ከእርሷ የተወለደው መሲሕ ክርስቶስም የባሕርይ አምላክ መሆኑን አላወቀም ነበር፡፡ ይህንን

(273) ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ *ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣* (አዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1987 ዓ.ም.)፣ ገጽ 12-13፡፡ ኤራቅሊስ በእንተ ትሥግእተ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ *ሃይማኖተ አበው፣* ገጽ 164-165፡፡ *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 71፡፡ አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ *ክብረ ድንግል፣* ገጽ 4፡፡ Gaventa, *Mary: Glimpses of the Mother of Jesus*. 41-42.

አስመልክቶ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ሲናገር "ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት÷ ወድቀውም ሰገዱለት፤ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅ፣ ዕጣንና ከርቤ አቀረቡለት::" (ማቴ. 2÷11) በማለት መስክሮአል::

የዚህ ገጸ በረከት ምሥጢራዊ ትርጓሜም ወርቁ በኤፍራታ ቤተ ልሔም ከድንግል ማርያም የተወለደውና በከብቶች ግርግም የተኛው መድኅን ክርስቶስ ንጉሠ ባሕርይ፣ ጽሩየ ባሕርይ የሆነ አምላክ መሆኑን ይገልጻል:: ከዚህም ጋር ሕፃኑ በባሕርይው ሞት ሽረት፣ በመንግሥቱ ኅልፈትና ውላጤ የሌለበት ሰማያዊና ዘለዓለማዊ ንጉሥ መሆኑንም ያስረዳል:: ዕጣኑ ደግሞ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሲል ራሱን ያማረና የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ዕፀ ሕይወት ወዕፀ መድኃኒት በሆነው መስቀል ላይ የሚፈጽመውን ክህነታዊ አገልግሎት ያጠይቃል:: ከዚህም ሌላ ሕፃኑ ምዑዘ ባሕርይ የሆነ አምላክ እንደሆነ በምሥጢር ያስተረጉማል::

በመጨረሻም ከርቤው የመድኃኒታችንን መከራውንና ሕማሙን፣ ስቅለቱንና ሞቱን ያመለክታል:: ይኸውም ከርቤ መራራ እንደሆነ ሁሉ፤ መፍቀሬ ሰብእ የሆነው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ በነሣው ሥጋና ነፍስ መራራ የሞት ጽዋን በፈቃዱ ተቀብሎ ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት በፍዳና በመርገም ተይዞ የነበረውንና በኃጢአትና በበደል የመረረውን የሰው ልጆችን ሕይወት አጣፍጦአል:: (ዮሐ. 19÷39-40)

ሌላው ምሥጢር ደግሞ ከርቤ የተለያየውን አንድ እንደሚያደርግና የተሰበረውንም እንደሚጠግን ሁሉ፤ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ ማርያም ተገልጦ፣ በዚህ ዓለም ተመላልሶ በፈጸመው አምላካዊ የቤዛነት ሥራ ከፈጣሪው አንድነት፣ ከሰማያውያን መላእክት ኅብረት ተለ ይቶ፣ በመንጸፈ ደይን ወድቆ፣ በእግረ አጋንንት



ሲጠቀጠቅ የነበረውንና በቍስለ ነፍስ ኃጢአት ተይዞ ደዌ ነፍስ የጸናበትን የሰውን ልጅ ጽንዐ ነፍስን ሰጥቶ ወደ ቀደመ ጸጋና ክብሩ መመለሱን ያስገነዝባል::[274]

ሁለተኛው ደግሞ አረጋዊው ቅዱስ ዮሴፍ እመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ የመሆኗን ምሥጢር የተረዳው ብርሃናዊው ኮከብ ከሰማይ ዝቅ፣ ከመሬት ብቅ ብሎ ሰብአ ሰገልን ከሩቅ ምሥራቅ እየመራ ወደ ኤፍራታ ቤተ ልሔም ማድረሱን በማየቱ ነው:: ስለሆነም መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ህልውና ለማወቅና ለመረዳት ምስክር የሚሆኑና የፈጣሪን መኖር ወደማወቅ መርተው ሊያደርሱ የሚችሉ ፍጥረታት መሆናቸውን በገለጠው መሠረት በዚህች ክብርት ዕለተ ልደትም ተፈጥሮአዊ ብርሃን የተሰጠው ኮከብ ሰብአ ሰገልን እየመራ ፈጣሬ ብርሃናት፣ አምላከ ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም ትሕትና ወደተኛባት ወደ ቤተ ልሔም ግርግም አድርሶአቸዋል::[275]

በዚህም ምሥጢር አማካይነት ቅዱስ ዮሴፍ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም እመ ብርሃን፣ እሙ ለፀሐየ ጽድቅ መሆኗን፤ ከእርሷ በተዋሕዶ የተወለደው አምላክ ደግሞ አማናዊ ብርሃነ ሕይወት፣ ፀሐየ ጽድቅ መሆኑን ተረድቷል፣ ተገንዝቦአል:: ወንጌላዊ "እነሆም በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ቦታ ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር:: ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው:: ወደቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት" (ማቴ. 2÷9-11) ሲል እንደመሰከረ::

በሦስተኛ ደረጃ የምንመለከተው ደግሞ አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ ታላቁን የጌታ ክብር መታየትና መገለጥ ተረድቶ ባየ ጊዜ

---

(274) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 129-130:: *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 75:: Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers,* 50.

(275) *መጽሐፈ ልደታ ["The Book of the Nativity of St. Mary"]* ed. Marius Chaine, *Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium,* vol. 7, *Scriptores Aethiopici,* 15-16.

እመቤታችን ድንግል ማርያም ማኅደረ መለኮት፣ መዝገበ ቃል፣ እመ እግዚአብሔር መሆኗን ማወቁንና መረዳቱን ነው:: ይህንን አስመልክቶ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ «... የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ» (ሉቃ. 2÷9) በማለት አስረግጦ ተናግሮአል:: ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊትም አስቀድሞ «ፈለግ ዘይውኅዝ ያስተፌሥሐ ሀገረ እግዚአብሔር፤ የወንዝ ፈሳሾች የእግዚአብ ሔርን ከተማ ደስ ያሰኛሉ::» (መዝ. 45÷4) ሲል በመዝሙሩ የተናገረው ቃለ ትንቢት በዚህች ታላቅና ልዩ ዕለት የብርሃን ጎርፍ በኤፍራታ ቤተ ልሔም ዙሪያ እንደ ጅረት በመፍሰሱ ምክንያት ተፈጽሟል::

ቅዱስ ዮሴፍ የድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት ያወቀበትና ያስተዋለበት አራተኛው ምክንያት ፍርሃተ ኖሎትን (የእረኞችን ፍርሃት) በማየቱና በመመልከቱ ነው:: ይኸውም ሊቀ ኖሎት (የእረኞች አለቃ) የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኤፍራታ ቤተ ልሔም በተወለደባት በዚህች ንዕድና ክብርት ዕለተ ልደት መንጋቸውን በሌሊት ነቅተውና ተግተው በሜዳ ሲጠብቁ ያደሩ እረኞች የተገለጠውን አምላካዊ ምሥጢርና ሰማያዊ ጸጋ አይተው በመደነቅ ታላቅ ፍርሃትን ፈርተው ነበር:: ይሁን እንጂ ሰማያዊው የጌታ መልአክ ወደ እረኞቹ ቀርቦ «እነሆ÷ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና» (ሉቃ. 2÷9-11) ሲል አጽናና ቸው፣ አረጋጋቸው:: አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍም ይህንን የኖሎት ፍርሃት አይቶ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአማን እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ መሆኗን አወቀ፣ ተረዳ:: ዳግመኛም ከእርሷ የተወለደው ሕፃን አምላክ፣ ወልደ አምላክ መሆኑንም ተገነዘበ::

አምስተኛውና የመጨረሻው ምሥጢር ደግሞ አረጋዊው ቅዱስ ዮሴፍ ሰማያዊው አምላክ ምድራዊ በሆነባት ዕለት በብርሃነ ልደቱ ፈጽመው የተደሰቱ ልዑላን መላእክትና ትሑታን ኖሎት አንድ



ማኅበር፣ አንድ መንጋ ሆነው «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ፤ በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን፤ በምድርም ሰላም ለሰው ልጅ በጎ ፈቃድ ይሁን» (ሉቃ. 2÷14) በማለት በታመነ የእውነት ቃል ያመሰገኑትን አዲስ ምስጋና ሰምቷል:: ይህም ልዩ ቃለ ውዳሴ ከዚህ በፊት ተሰምቶ የማይታወቅ ልዩ የአዲስ ኪዳን ምስጋና ነው:: የቤተ ክርስቲያናችን የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ይህን ምሥጢር ሲያደንቅ «ዮም አሐደ መርዔተ ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ ንጉሥ በቃለ አሚን»፤ ሰማያዊው አምላክ በግርግም ተኝቶ በታየባትና በተገለጠባት በዛሬዋ ዕለት ልዑላን የሆኑ ቅዱሳን መላእክትና ትሑታን የሚሆኑ ኖሎት (ደቂቀ አዳም) ንጉሥ ክርስቶስን በታመነ የእውነት ቃል ፈጽመው ያከብሩትና ያመሰግኑት ዘንድ አንድ መንጋ፣ አንድ ማኅበር ሆኑ በማለት ዘምሯል::

አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍም ይህን ታላቅ ምሥጢር አይቶ በኤፍራታ ቤተ ልሔም ከድንግል ማርያም የተወለደው ሕፃን እግዚአ ስብሐት፣ እግዚአ ውዳሴ ማለት የምስጋናና የክብር ባለቤት መሆኑን ተረዳ:: በዚህም መሠረት ይህንን ኃያል ጌታ የወለደች እመቤታችን ድንግል ማርያም እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ እንደሆነች አውቆ ተረድቷል::

ቀደም ብለን እንደገለጥነው የቤተ ክርስቲያን መተርጉማን ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ «የበኩር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም» (ማቴ. 1÷25) ሲል የተናገረውን ገጸ ንባብ አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ በቅደም ተከተል የጠቀስናቸውን አምስት ነገሮችን ማለትም:-

- ምጽአተ ሰብአ ሰገል ዘምስለ አምኃ፣
- ሑረተ ኮከብ በካልአ ፍና፣
- ሥርቀተ ስብሐተ እግዚአ ዐቢይ፣
- ፍርሃተ ኖሎትን፣ እንዲሁም
- ቀዳሴ መላእክትን

አይቶ እስኪረዳ ድረስ የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት፣ እንዲሁም የልጇ የወዳጇ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አላወቀም፣ አልተረዳም፣ አላስተዋለም ብለው አስማምተው ተርጉመውታል::

ከዚህም ጋር ጻድቁ ዮሴፍ እመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ የመሆኗን ምሥጢር አስቀድሞ ቅዱሳን አበው በብዙ ዓይነት ኅብረ አምሳል የመሰሉላት፣ ቅዱሳን ነቢያትም በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢት የተናገሩላት መሆኗን አላወቀም፣ አልተረዳም ማለት ነው:: ዳግመኛም ቅዱስ ዮሴፍ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ስለ ሥጋዌው ምሥጢር የተመሰለለት ኅብረ አምሳል፣ የተነገረለት ኅብረ ትንቢት በዕለተ ልደት ተፈጽሞ እስኪያይ ድረስ አልተገነዘበም፣ አላስተዋለም:: ዳግመኛም ስለ መሲሕ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣትና ከድንግል ማርያም ሰው መሆን የተነገረው ትንቢት ቀረ፣ የተቆጠረው ሱባኤ ግን ደረሰ እያሉ ከሚያዝኑት አንዱ ይህ አረጋዊ ዮሴፍ ነበር::

በዚያውም ላይ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፈ ትንቢት ይመለከት ነበርና «ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች፤ እግዚአብሔር ወልድንም በድንግልና ትወልዳለች» (ኢሳ. 7÷14) የሚለውን ተስፋ ትንቢት ያውቅ ስለነበር ከዘመኑ ደርሶ ሳለ ያልደረሰኩ መስሎት ድንግል የተባለች እርሷ (ቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም)፣ ወልድ የተባለ ደግሞ እርሱ (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) እንደሆነ ከላይ የተገለጹትን አምስት ነገሮች አይቶ እስኪረዳ ድረስ ኢያእመረ (አላወቀም) ማለት ነው::[276] ይህንን አስመልክቶ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ሲጽፍ «ዮሴፍና እናቱም ስለ እርሱ በተባለው ነገር ይደነቁ ነበር» (ሉቃ. 2÷33) ብሏል::

(276) ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ *ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ*፣ ገጽ 12-13:: *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 71:: አንዱዓለም ዳግማዊ፣ *ክብረ ድንግል*፣ ገጽ 4:: St. Jerome, *St, Mary the Ever Virgin*, 12. Graef, *Mary: A History of Doctrine and Devotion*, 74-76.



ከላይ በዝርዝር በገለጥነው የቅዱሳት መጻሕፍት አማናዊ ምስክርነትና የኦርቶዶክሳውያን አበው ቀጥተኛ ትምህርት መሠረት አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ ከላይ የገለጥናቸውን የሥጋዌ ምሥጢራት በዕለተ ልደት በግልጽ አይቶ ከተረዳና ካስተዋለ በኋላ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗን በሚገባ አውቋል:: ዳሩ ግን ቅዱስ ዮሴፍ ይህን ሁሉ ምሥጢር ካየና ካስተዋለ በኋላ የፈጣሪው እናት፣ የጌታው አማናዊት ቤተ መቅደስና ታቦት የሆነችውን ቅድስት ድንግል እመቤታችንን ለመቅረብ ተደፋፍሮአል የሚለው ሔልቪዲየሳዊ የክሕደት አስተሳሰብና የድፍረት አነጋገር ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ከመሆኑም በላይ ጽርፈትም (ዘለፋም) ነው::[277]

ከዚህም ጋር ልናስተውለውና ልንገነዘበው የሚገባን ዐቢይ ምሥጢር ደግሞ ቅዱስ ዮሴፍ አማናዊት ታቦተ እግዚአብሔር የሆነችውን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለመቅረብ፣ ለመዳሰስ፣ ለመንካት ተደፋፍሮ ቢሆን ኖሮ ዕድል ፈንታው፣ ጽዋዐ ተርታው እንደ ዖዛ ወልደ አሚናዳብ በሆነ ነበር:: (2ኛ ሳሙ. 6÷1-10፤ 1ኛ ዜና 13÷6-12) ቅዱስ መጽሐፍ ይህንን አስመልክቶ ሲናገር «... ታቦቱን ሊይዝ ዖዛ እጁን ዘረጋ:: የእግዚአብሔርም ቁጣ በዖዛ ላይ ነደደ÷ እጁንም ወደ ታቦቱ ስለዘረጋ ቀሠፈው፤ በዚያም በእግዚአብሔር ፊት ሞተ::» (1ኛ ዜና 13÷9-10፤ 2ኛ ሳሙ. 6÷6-7) በማለት በግልጥ ይመሰክራል::

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በጸጋ በሚያድርባትና በረድኤት በሚገለጥባት በታቦተ ጽዮን የተመሰለችበትንና አማናዊት ታቦተ ጽዮን የተባለችበትን ምሥጢር ወደፊት በምናየው በምዕራፍ አምስት ውስጥ በስፋት እንመለከታለን::

(277) Hainsworth, "*The Ever-Virginity of the Mother of God,*" 2. Pope Shenouda III, *Comparative Theology*, 180. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 12. Pope Shenouda III, *The Perpetual Virginity of the Virgin St. Mary*, 8.

### 4.1.6.3 «የጌታ ወንድሞች» የተባሉት እነማን ናቸው? ለምን?

በዚህ ንዑስ ክፍል በቅዱስ ወንጌልና በመልእክታት ውስጥ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሞችና እኅቶች ተብለው የተጠቀሱት እነማን እንደሆኑና የተጠቀሱበትን ምክንያት በአጭሩ እንመለከታለን:: በመጀመሪያ ደረጃ ቀደም ብለን በክፍል 4.1.6.1 እና 4.1.6.2 ሥር የዘረዘርናቸው ገጸ ንባባት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ በሚያስተምርበት ወቅት የነበሩት አይሁድ ስለ እርሱ ማንነት የነበራቸውን የተሳሳተ አመለካከት በግልጥ ያስረዳሉ:: ይኸውም ወንጌላውያን እንደገለጹት እኒህ አይሁድ ስለ መሲሕ ክርስቶስ ማንነት የነበራቸው አስተሳሰብ ትክክለኛ አልነበረም:: ምክንያቱም ክብር ምስጋና ይግባውና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከዮሴፍና ከእመቤታችን የተወለደ ዕሩቅ ብእሲ (ፍጡር) አድርገው በተሳሳተ መንገድ ይመለከቱት ስለነበር ነው::

ይህንን አስመልክቶ ወንጌላውያን ሲናገሩ:- «ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን? እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ተሰናከሉበትም» (ማቴ. 13÷53-55)፤ «እንደመሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ ...» (ሉቃ. 3÷23) «... አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው ይህ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን?» (ዮሐ. 6÷42) በማለት አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ማን ብለው ይረዱት እንደነበር በግልጽ መስክረዋል:: ይልቁንም ደግሞ አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ እመቤታችንን በአደራ ከመቀበሉ በፊት በጋብቻ አብራው ከነበረችውና በሞት ከተለየችው ሚስቱ የወለዳቸው ልጆች እንደነበሩት በአይሁድ ዘንድ የታወቀና የተረዳ እውነታ ነው::

ይሁን እንጂ ከላይ እንዳየነው አይሁድ ጌታን ወልደ ዮሴፍ ይሉት ስለነበር የእመቤታችን የድንግል ማርያም ጠባቂ የነበረው ቅዱስ



ዮሴፍ ከሟች ሚስቱ የወለዳቸውን ልጆቹን የጌታ ወንድሞችና እኅቶች እንደሆኑ አድርገው ተናገሩ እንጂ ከእመቤታችን የተወለዱ ሆነው አይደለም:: ስለሆነም መምህረ ቅዱሳን ኢየሱስ ክርስቶስ «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ» (ማቴ. 22÷29) ሲል እንዳስገነዘበው ዛሬም እኛ በመጀመሪያ ይህንን ቃል የተናገሩት እነማን ናቸው? ለምንስ እንዲህ አሉ? ብለን ልንጠይቅና በማስተዋል ልንመረምር ይገባናል::

በመሠረቱ «ወንድሞቹ፣ እኅቶቹ» የሚለውን ቃል የተናገሩት መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ማንና የማን ልጅ እንደሆነም በሚገባ ጠንቅቀው ያልተረዱና በትክክል ያላመኑ አይሁድ ናቸው:: ከላይ የጠቀስነውና ወንጌላውያን የሰጡትን አማናዊ ምስክርነት በማስተዋል ስንመለከተው አይሁድ ጌታን «ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን?» ሲሉ እውን ጌታ ደኃራዊ ለሆነው ሥጋዊ ልደቱ በምድር አባት ኖሮት ይሆንን? ይህማ እንዳይባል ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ «የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ:: እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች» (ማቴ. 1÷18) በማለት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደኃራዊ ልደቱ በምድር አባት እንደሌለው አስረግጦ አስረድቷል፣ አስገንዝቧል፣ መስክሯል::

ታዲያ አይሁድ ጌታን የጸራቢው የዮሴፍ ልጅ ነው ብለው መናገራቸው እውነተኞች ያሰኛቸዋልን? ይህ ዓይነቱ ከንቱ ንግግራቸውስ ትክክለኛ አማኞች ያደርጋቸዋልን? ይህንንም ወንጌላዊው «ተሰናከሉበትም» (ማቴ. 13÷56) በማለት ይህ የአይሁድ አነጋገር ፍጹም ስሕተትና ፀርፈት (ስድብ) መሆኑንም በግልጥ መስክሮአል:: በዚህም ምክንያት «በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው» (ማቴ. 11÷6) ከሚለው አምላካዊ ቃለ በረከት ውጭ መሆናቸውን ልብ ይሏል::[278]

---

[278] *መጽሐፈ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 450:: *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 71:: አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን) *ክብረ ድንግል፣* ገጽ 4:: St. Jacob of Serug, *On the Mother of God,* 61. Harakas, *Exploring Orthodox Christianity:*

ዳግመኛም ቅዱስ ወንጌል አይሁድ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወልደ ዮሴፍ በማለታቸውና አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ በሞት ምክንያት ከተለየችው ሚስቱ የወለዳቸውን ልጆቹን ደግሞ የጌታ ወንድሞችና እኅቶች እንደሆኑ አድርገው በመቁጠራቸው ከእውነተኞች ምእመናን ወገን የተለዩ መሆናቸውን ሲገልጥ «በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም» (ማቴ. 13÷58) በማለት በአጽንኦት ተናግሮአል:: ከዚህም ጋር ይህ ኃይለ ቃል አይሁድ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በትክክል እንዳላወቁና እንዳልተረዱ፣ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑንም በትክክል እንዳላመኑ ያስረዳል፣ ያስገነዝባል፣ ያረጋግጣልም::

ዛሬም ቢሆን በዘመናችን ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ «በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና» (ሮሜ 15÷4)፤ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው:: ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ» (ዕብ. 13÷8-9) ሲል እንዳስገነዘበው ከላይ በገለጥነው የአይሁድና የሔልቪዲየሳውያን የስሕተት ትምህርት ተሳስተው በክሕደት ጉዳና የሚጓዙ ወገኖች አልጠፉም:: ቁም ነገሩ ግን ከላይ እንደገለጥነው አይሁድ ጌታን የዮሴፍ ልጅ ነው ይሉት ስለነበረ የዮሴፍን ልጆች ወንድሞቹና እኅቶቹ ናቸው አሉ እንጂ ዳሩ የእናቱ የድንግል ማርያም ልጆች አላሉም:: ለዚህም በማቴዎስ 13÷55 ላይ ስማቸው የተጠቀሰው ያዕቆብና ይሁዳ ራሳቸው በጻፏቸው መልእክታት ላይ የሰጡት አማናዊ ምስክርነት በቂ ማስረጃና ማረጋገጫም ነው::

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ መልእክቱን ሲጀምር «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ ...» (ያዕ. 1÷1) በማለት የፈጣሪውና የአምላኩ

*Orthodox Christian Belief About the Bible: Real Answers to Real Questions from Real People*, 115-116, 138. Ware, *The Orthodox Church*, 258. Gaventa, *Mary: Glimpses of the Mother of God*, 12. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 16. Pope Shenouda III, *The Perpetual Virginity of the Virgin St. Mary*, 9-10.



የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና አገልጋይ መሆኑን ገልጾ አስረዳ እንጂ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም የሆነ ያዕቆብ አላለም:: ዳግመኛም ሐዋርያው ይሁዳ «የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ፣ የያዕቆብም ወንድም የሆነ ይሁዳ ...» (ይሁዳ 1÷1) ሲል ራሱን የያዕቆብ ወንድም አለ እንጂ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም አላለም:: ይልቁንም መምህረ ቅዱሳን የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ባሪያና አገልጋይ፣ እውነተኛ ሐዋርያ መሆኑን ገልጾ መሰከረ እንጂ:: ስለዚህም እንደ አይሁድና እንደ ሔልቪዲየስ አባባል ያዕቆብና ይሁዳ ምስጋና ይግባትና ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም የተወለዱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋ ወንድሞቹ ቢሆኑ ኖሮ ይህንን እውነታ በመልእክታቸው ገልጸውና ጠቅሰው በተናገሩ ነበር:: ከላይ እንዳየነው ግን ሁለቱም የፈጣሪያቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትና አገልጋዮች መሆናቸውን አስረግጠው መስክረዋል::

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ለሔልቪዲየሳዊ የክሕደት ትምህርት መጠነ ሰፊ የሆነ ምላሽ በሰጡበት የነገረ ማርያም የምሥጢር መድበል «የጌታ ወንድሞች» ተብለው የተጠቀሱት ከእመቤ ታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለዱ አለመሆናቸውን በግልጥ አስረድተዋል:: ከዚህም ጋር የጌታ ወንድሞችና እኅቶች የተባሉበት ሌ ላው ምክንያት ደግሞ በዕብራውያን ባሕልና ሥርዓት መሠረት የወንድም ልጅ፣ የእኅት ልጅ፣ የአክስት ልጅ፣ የአጎት ልጅ፣ የቅርብ ዘመድና አብሮ አደግ የሆነ ሁሉ ወንድም እኅት ይባል ስለነበረ ነው:: ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍትን ምስክርነት መሠረት በማድረግ ወንድማማችነትን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለው አስተ ምረዋል:: እነዚህም:-

- በሥጋዊ ልደት ላይ የተመሠረተ ወንድምነት፣
- በዘር ሐረግ ወይም በደም ትሥሥር ላይ የተመሠረተ ወንድምነት፣

- **በአንድ ዓይነት ቤተሰባዊ ሐረግ ላይ የተመሠረተ ወንድምነት** እና
- በመንፈሳዊ ፍቅርና ጓደኝነት ወይም ወዳጅነት ላይ የተመሠረተ ወንድምነት ናቸው::(279)

ከላይ የዘረዘርናቸውን የወንድማማችነት ዓይነቶች በቅዱስ መጽሐፍ ማስረጃነት ለማየትና ለመግለጽ ያህል የመጀመሪያው ወንድምነት እንደ አቤልና ቃየል (ዘፍ. 4÷1-2)፣ ያዕቆብና ኤሳው (ዘፍ. 25÷21-26)፣ ጴጥሮስና እንድርያስ (ማቴ. 4÷17-18) ያለውና በሥጋዊ ልደት ላይ የተመሠረተው ወንድማማችነት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በአንድ ዓይነት የዘር ሐረግ ወይም የደም ትሥሥር ላይ የተመሠረተው የሕዝበ አይሁድ (እስራኤላውያን) ወንድማማችነት ነው:: (ዘዳ. 15÷13፤ 17÷15፤ 22÷1፤ ሮሜ 9÷3-4):: ሦስተኛው የወንድምነት ዓይነት በአንድ የቤተሰብ ሐረግ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሰዎች መካከል ያለው ቤተሰባዊ ወንድማማችነት ነው:: (ዘፍ. 13÷8፤ 11÷27፤ 14÷4-5፤ 14-16፤ 29÷15):: አራተኛውና የመጨረሻው የወንድምነት ዓይነት ደግሞ በመንፈሳዊ ልደትና ፍቅር ላይ የተመሠረተ መንፈሳዊ ወንድማማችነት ነው:: (መዝ. 132÷1፤ 21÷22፤ ዮሐ. 20÷17፤ 1ኛ ቆሮ. 50÷11፤ ሮሜ 12÷1)

ከእነዚህ አራት የወንድማማችነት ዓይነቶች መካከል «የጌታ ወንድሞችና እኅቶች» የሚለው አገላለጽ በሦስተኛው የወንድማማችነት ዓይነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ይገነዘቧል:: ለአብነት ያህል ብንጠቅስ:-

- በዘፍጥረት 13÷8 ላይ «አብርሃምም ሎጥን አለው:- እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ

(279) Sheen, *The World's First Love*, 51-54. St. Jerome, *St. Mary the Ever Virgin*, 19-23. Pope Shenouda III, *The Perpetual Virginity of the Virgin St. Mary*, 9-10. St. Jerome, "The Perpetual Virginity of Blessed Mary," 341-343. Pope Shenouda III, *Comparative Theology*, 181-182. አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ *ክብረ ድንግል*፣ ገጽ 4::



መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ» አለው ተብሎ ተጽፎ አል:: እንግዲህ እንደ አይሁድና እንደ ሔልቪዲየሳውያን አመለካከት ወንድም የሚባለው የግድ ከአንድ እናትና አባት የተወለደ ብቻ ነው ከተባለ የአብርሃምና የሎጥ ወላጆች በየት ይገናኛሉ? ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ አብርሃም የሎጥ አጎት እንደሆነና ሎጥ ደግሞ የአብርሃም የወንድም ልጅ መሆኑን በግልጽ ይመሰክራልና ነው:: (ዘፍ. 11÷27፤ 12÷4-5፤ 14÷14-16)

- ሌላው ደግሞ በዘፍጥረት 29÷15 ላይ «ላባም ያዕቆብን:- ወንድሜ ስለሆንህ በከንቱ ታገለግለኛለህን?» አለው ይላል:: በዚህ የቅዱስ መጽሐፍ ክፍለ ንባብ ደግሞ ላባ ያዕቆብን /የእኅቱን የርብቃ ልጅ/ ወንድሜ ብሎ እንደጠራው ልብ ይሏል::
- ከዚህም ጋር በዘሌዋውያን 10÷4 ላይ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከናዳብና ከአብዩድ ሞት በኋላ «የአሮንን አጎት የዑዝኤልን ልጆች ሚሳኤልንና ኤልጻፋንን ጠርቶ:- ቅረቡ ወንድሞቻችሁንም ከመቅደሱ ፊት አንሥታችሁ ከሰፈር ውጭ ውሰዱአቸው» በማለት ተናግሮአል:: ከዚህ ገጸ ንባብ በዕብራውያን ልማድ በአንድ ቤተሰባዊ ጥላ ሥር ያሉ ወገኖች ሁሉ ወንድማማች ተብለው እንደሚጠሩ ይመለከቷል::

የቤተ ክርስቲያናችን መተርጉማን ለሔልቪዲየስና ተከታዮቹ የሰጡት ሌላው መሠረታዊ ምላሽ ደግሞ በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ እግረ መስቀል ሥር የተከናወነውን አምላካዊ የአደራ ስጦታ ምስክር ያደረገ ነው:: ይኸውም በዮሐንስ 19÷26-27 ላይ «... ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት:: ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን:- እናትህ እነኋት አለው:: ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት» ተብሎ እንደተገለጸው የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ በማዕከለ ምድር በቀራንዮ መልዕልተ መስቀል ሳለ

(መዝ. 73÷12) አደራ በሚሰጥ ሰው ቋንቋ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን “እነኋት እናትህ” ብሎ ለሚወደው ደቀ መዝሙሩና እስከ እግረ መስቀል ድረስ ሳይለይ ለተከተለው ታማኝ ሐዋርያ ለቅዱስ ዮሐንስ መንፈሳዊ እናት እንድትሆነው በአደራ ሰጥቷል:: በአንጻሩ ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስን ለድንግል ማርያም መንፈሳዊ ልጅ ይሆናት ዘንድ አምላካዊ አደራውን አስተላልፏል::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን ለሚወደው ደቀ መዝሙሩ ለቅዱስ ዮሐንስ አደራ መስጠቱ እመቤታችን ከልጇ ከወዳጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ ልጅ ፈጽሞ እንዳልነበራት በግልጥ ያስረዳል፣ ያስገነዝባልም:: ምክንያቱም እንደ አይሁድና ሔልቪዲየሳውያን አባባል ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከአንድያ ልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ልጆች ቢኖሯትማ ኖሮ በዕለተ ዓርብ በጌታችን መስቀል አጠገብ በተገኙ ነበር:: ዳግመኛም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ድንግል ማርያምን በመስቀሉ ሥር ቆማ ባያት ጊዜ እነዚያ ልጆችሽ (ማለትም ወንድሞቼና እኅቶቼ) ይርዱሽ፣ ያገልግሉሽ ይላታል እንጂ እናቱን ለደቀ መዝሙሩ አደራ አይሰጥም ነበር:: ዳሩ ግን እመቤታችን ድንግል ማርያም አንድያ ልጇ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ በመሆኑና ሌሎች የሥጋ ወንድሞችም ሆኑ እኅቶች ፈጽሞ ስላልነበሩት እናቱን ለሚወደውና እስከ መስቀል ድረስ ታማኝ ለሆነው ሐዋርያ ለቅዱስ ዮሐንስ በአደራ ሰጥቷል::[280]

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ መሠረት እመቤታችን ድንግል በክልኤ (በሥጋም በነፍስም /በኀሊናም) ድንግል መሆኗን ተመልክተናል:: ስለሆነም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሐልዮ (በማሰብ)፣ በነቢብ (በመናገር)፣

(280) Baggley, *Festival Icons for the Christian Year,* 100-101. Gambero, *Mary and the Fathers of the Church: The Blessed Virgin Mary in Patristic Thought,* 178. Hainsworth, "The Ever- Virginity of the Mother of God," 3-4. አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 157:: አንዱዓለም ዳግማዊ (ዲያቆን)፣ *ክብረ ድንግል*፣ ገጽ 5::



እንዲሁም በገቢር (በመሥራት) ኃጢአትና በደል የማታውቅ፤ ነውርና ነቀፋ የሌለባት ፍጽምት፣ ንጽሕት፣ ቅድስት፣ ኅትምት፣ ድንግል ናት:: ይህንንም ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና የመውለዷን ምሥጢር “እነሆም ትፀንሻለች እግዚአብሔር ወልድንም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ” (ሉቃ. 1÷31) ብሎ ባበሠራት ጊዜ እመቤታችን ድንግል ማርያም መልአኩን “ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?” (ሉቃ. 1÷34) ስትል መልሳለታለች:: ከዚህ የእመቤታችን መልስ ወላዲተ አምላክ ብሥራተ መልአክን እስከሰማችበት ጊዜ ድረስ ወንድ የማታወቅ ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በልዕልና መሆኗን፤ እንዲሁም ለወደፊ ቱም እስከ መጨረሻው ድረስ ወንድ ሳታውቅ በንጽሕና፣ በቅድስናና በድንግልና ጸንታ የምትኖር መሆኑን እንረዳለን፣ እንገነዘባለን::

ሌላው ደግሞ እመቤታችን ለወንድ ታጭታና ከወንድ ጋር ሳለች የዚህን ዓለም የሥጋ ፈቃድና ጠባይዓ አንስት (ልማደ አንስት) እንኳን በገቢር (በመሥራት) ቀርቶ በሐልዮ (በሐሳቧ) ማለት በኅሊናዋና በልቡናዋም ፈጽማ የማታውቅ፤ ንጹሐ ባሕርይ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር ወልድ እናትነት የለያትና የመረጣት፣ ለድኅነተ ዓለም ሥራም ልዩ መሣሪያ አድርጎ ያከበራትና ከፍ ከፍ ያደረጋት በሁለት ወገን ማለት በሥጋና በነፍስ ድንግል፣ ኅትምት መሆኗንም ልብ ይሏል:: እንግዲህ በአጭሩ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ሁለንተናዊ ዜና ሕይወት እንዲህ ከሆነ ሔልቪዲየሳውያን ወላዲተ አምላክ ከአንድያ ልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌሎች ልጆች አሏት ለማለት የሚያስደፍራቸው አንዳችም ምክንያት ሊኖር አይችልም፣ የለምም::

ኦርቶዶክሳውያን አበው “ተወልደ በተድላ መለኮት፤ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ለመለኮት በሚገባ ልደት ተወለደ” ሲሉ

በአንድነት ተናግረዋል:: ይህም ማለት እንበለ ዘርዕ፣ እንበለ ሩካቤ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ፣ በኅቱም ድንግልና ያለ አባት መወለድ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት ለተወለደው ለአካላዊ ቃል ለእግዚአብሔር ወልድ በእውነት የሚገባ ልደት ነው ማለት ነው:: በአንጻሩ ግን ወልደ እግዚአብሔር ለሥጋ በሚገባ ተፈጥሮአዊ ልደት ተወልዶ ቢሆን ኖሮ በዘር፣ በሩካቤ ተፈትሖ ማኅፀን ካላት ሴት በተወለደ ነበር::

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ለመለኮት የሚገባ ልደት የተከናወነባትን ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያምን በመጽሔተ ትንቢት እያያት ሲናገር «ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር፤ አንቺ የእግዚአብሔር አገር ሆይ በአንቺ የተደረገ የልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ሥራው ዕፁብ ድንቅ ነው» (መዝ. 86÷3) በማለት እመቤታችን ወልደ እግዚአብሔርን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና የመውለዷን ታላቅና ድንቅ ምሥጢር ገልጾ መስክሮአል:: አማናዊቷ ሀገረ እግዚአብሔር የሆነችው ድንግል ማርያምም በሉቃስ 1÷46-55 ላይ በተናገረችውና «መዝሙረ ድንግል» ተብሎ በሚጠራው የምስጋና ጸሎቷ «ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራን አድርጎአልና» (ሉቃ. 1÷49) ስትል በድንግልና ፀንሳ፣ በድንግልና እንድትወልደው የመረጣትና ያከበራትን አምላክ አመስግናለች::

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የተባለው የቤተ ክርስቲያናችን አባት «አንክሮጦስ» በተሰኘው መጽሐፉ የጌታ ወንድሞችና እኅቶች ተብለው በቅዱስ መጽሐፍ የተጠቀሱት ደቂቀ ዮሴፍ (የአረጋዊው ጻድቅ የቅዱስ ዮሴፍ ልጆች) መሆናቸውን በግልጽ አስረድቷል:: ዳግመኛም በክፍል 4.1.2 ላይ እንዳየነው በትረ አሮን ከነገደ እሥራኤል በትሮች ሁሉ በጥበበ እግዚአብሔር ተለይታና ተመርጣ፣ በሐመልማል ተንቈጥቍጣ፣ በጽጌ አጊጣ በማበቧና በማፍራቷ ምክንያት ካህኑ አሮን ደብተራ ኦሪትን ለማገልገል እንደታጨና እንደተመረጠ ሁሉ፤ እንደዚሁም በትረ ዮሴፍ ከነገደ ይሁዳ ወገን ከተሰበሰቡት በትሮች መካከል በጥበበ



እግዚአብሔር በማበቧና በመለምለሟ ምክንያት አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ አማናዊቷን ቤተ መቅደስ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለማገልገል በክብር ታጭቷል፣ ተመርጧልም::[281] በዚህም በበትረ አሮንና በበትረ ዮሴፍ፣ በደብተራ ኦሪትና በአማናዊት ቤተ መቅደስ በድንግል ማርያም መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር ይመለከቷል::

ምንም እንኳን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአረጋዊው ጻድቅ ለቅዱስ ዮሴፍ ብትታጭም ቅሉ የብፅዓት ልጅ በመሆኗ በእደ ብእሲ መዳሰስ፣ በዘር በሩካቤ መፅነስ የለባትም:: ከዚህም ጋር ቀደም ብለን እንደገለጽነው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ድኅረ ዓለም ወልደ እግዚአብሔርን ያለ አባት በመውለዷ ቅድመ ዓለም ያለ እናት የወለደው የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ ስለሆነች ከሥግው ቃል ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር የዕሩቀ ብእሲ (የፍጡር) እናት ልትሆን ፈጽሞ አትችልም::

ሌላው ደግሞ በክፍል 4.1.4 ላይ እንደተመለከትነው እመቤታችን ድንግል ማርያም ዓውደ ማኅፀኗ አስቀድሞ በትንቢተ ነቢያት ታጥሯል፣ ታትሞአል፣ በብፅዓት ተቀጥሯል፣ ለዘላለም ተዘግቶ ይኑር እንጂ አይከፈት፤ ሰውም አይግባበት የሚል አምላካዊ አዋጅ ታውጆበታል:: ዳግመኛም ሊቁ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ «ሥጋ የሌለው እርሱ ሥጋዋን ተዋሕዶ እንደ ሰው ሁሉ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በጌትነቱ ሳለ በማኅፀኗ ተወሰነ:: ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀንም ከተፈጸመ በኋላ ... በኅቱም ድንግልና ተወለደ፤ ማኅተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም»[282] በማለት በአጽንኦት ገልጾአል::

ዳግመኛም ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በአንድ ቃል «ኅትምት ክታብ፤ የታተመች ደብዳቤ» ["Sealed Document /Sealed Letter"]

---

(281) መጽሐፈ ሕዝቅኤል ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 450-451 ::
(282) ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ «በእንተ ምሥጢረ ሥላሴ»፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 212::

በማለት ጠርተዋታል። በዚህም ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ አስቀ
ድሞ «ማንበብንም ለሚያውቅ፦ ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ
እርሱ፦ ታትሞአልና አልችልም ይላቸዋል፤ ደግሞም መጽሐፉን ማን
በብን ለማያውቅ፦ ይህን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ፦ ማንበብ
አላውቅም ይላቸዋል» (ኢሳ. 29÷11-12) ብሎ የተናገረውን ቃለ ትንቢት
በምሥጢር ለእመቤታችን ተርጉመው ወስደውታል። ይኸውም ወላ
ዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ንጽሕና ቅዱስ የሆነውን አካሏን «ይኩነኒ
በከመ ትቤለኒ» ብላ በፈቃዷ ለፈጣሪዋ በሰጠች ጊዜ አካላዊ ቃል በማኅፀኗ
ሰሌዳ ላይ ተቀርጿል።

ይህ ረቂቅና ድንቅ አምላካዊ ምሥጢር የተፈጸመባት እመቤ
ታችንም «አንተ ይእቲ መጽሐፍ ኅትምት ዘኢተርኅወ ማኅተመ ሥጋዩ ዘስፈ ሰጸው
በመናስግተ ድንግልና» ስትል ለጠባቂዋ ለቅዱስ ዮሴፍ ገልጻ አስ
ረድታዋለች። ስለሆነም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም አካላዊ
ቃል እግዚአብሔር ወልድ በንጽሕና የተጻፈባት፤ የእግዚአብሔር
ይቅርታ፣ ምሕረትና ቸርነት ለሰው ልጅ የተላከባትና ይህ አምላካዊ
ጸጋና በረከት ለመላው ዓለም የተላለፈባት ኅትምት ደብዳቤ (መጽሐፍ)
ናት። ዳግመኛም እመቤታችን የይቅርታና የሕይወት ደብዳቤ ናት
መባሏ ከተጻፈች በኋላ የታተመች ሆና አይደለም። ይልቁንም በማይመ
ረመር ረቂቅና ድንቅ የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጥበብ እንደታተ
መች (በኅቱም ድንግልና ጸንታ ሳለች) ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር
በማኅፀኗ ሰሌዳ ተጻፈ፣ ተፀነሰ እንጂ። ከዚህም ጋር ኅትምት ጦማ
ፈ ሕይወት ወመዝገበ በረከት የሆነችው ድንግል ማርያም ሳትከፈት
በመጽሔተ መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንደተነበበች ልብ ይሏል።(283)

(283) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis Di Sagla], "መጽሐፈ ምሥጢር" *[Ii Libro Del Mistero]*፣ ገጽ 9-10፣ 88:: St. Jacob of Serug, *On the Mother of God*, 37-39, 44, 60. Brock, *Bride of Light*, 118. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 41. ቅዱስ ሳዊሮስ፣ «ስለ ኒቅያ ሃይማኖት»፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 357፣ 361:: ቅዱስ ያሬድ፣ «አንቀጸ ብርሃን»፣ ገጽ 403:: ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፣ ገጽ 16-17:: Davis, *The Seven Ecumenical Councils (325-787): Their History and Theology*, 244.



በመሆኑም የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ የበዛላቸው
ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን፦

«ማርያም ፊደል የሁሉ መማሪያ፣
በንጽሕና በቅድስና ተጽፋለችና።»

እያሉ ዘወትር ከሚያከብሯትና ከሚያመሰግኗት ምስጋና ጋር
በምሥጢር የተገናዘበና የተሰናሰለም ነው።

ከዚህ በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስን የተመላች ቅድስት ኤ
ልሳቤጥ ቃሏን አሰምታ «ወምንትኑ አነ ከመ ትምጽኢ ኀቤየ እሙ ለእግዚእየ፤
የጌታዬ፣ የአምላኬ፣ የፈጣሪዬ የኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ እመቤቴ አንቺ
ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድን ነኝ?» (ሉቃ. 1÷43) ስትል
በትሕትና የተናገረችው ከሣቴ ምሥጢር የሆነው እግዚአብሔር
መንፈስ ቅዱስ በኅቱም ማኅፀነ ድንግል ማርያም የተቀረጸውን የአካላዊ
ቃል ህልውና ስለገለጸላት ነው።

በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የሚዘመረው
የእመቤታችን ምስጋና ይህንን ታላቅ ምሥጢር አስመልክቶ ሲናገር
«አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ብቻ የገባብሽ፣ ሳይከፍት ገብቶ
ሳይከፍት የወጣብሽ ልዩ ደጃፍ ሆይ ክብርና ምስጋና ይገባሻል»(284)
ይላል። ዳግመኛም ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ በነገረ ማርያም የምሥጢር
መድበሉ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን «በእሳታዊ ቁልፍ የተ
ዘጋች በርና የተቆለፈች ደጅ»(285) በማለት ማኅተመ ድንግልናዋ
በሥልጣነ መለኮት የታፈረና የተከበረ መሆኑን በአጽንኦት አስረድቷል፣
አስገንዝቧል።

እንግዲህ በአጠቃላይ በዘመነ ብሉይ በቅዱሳን አበው በኩል በተ
ለያየ ኀብረ አምሳል የተገለጠው፣ በቅዱሳን ነቢያት አማካይነት በብዙ

(284) Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept*, 11.
(285) *Brock, Bride of Light*, 140.

ዓይነት ኅብረ ትንቢት የተነገረውና ኋላም በዘመነ ሐዲስ በቅዱሳን ሐዋርያት አማናዊ ቃል የጸደቀውና ከሊቃውንት አበው የምሥጢር ምንጭ የፈለቀው ቀጥተኛው እምነትና ትክክለኛው ትምህርት ይህ ነው:: ይሁን እንጂ መጽሐፍ «ከተጻፈው አትለፍ» (2ኛ ቆሮ. 4÷6) በማለት እንዳስገነዘበው ከዚህ አማናዊ አስተምህሮ አልፎና ተርፎ ቅዱሳት መጻሕፍት አምላካውት ባልሔዱበት የስሕተት መንገድ ገስግሶ፣ በተለያዩ ኅብረ አምሳል የተመሰለውን ምሳሌ አፍርሶ፣ በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢት የተነገረውን ተስፋ ጥሶ፣ እንግዳ በሆነ የኑፋቄ ትምህርት ማዕበል መወሰድ ወደ ጽኑ የክሕደት ጉድጓድ የሚጥል አስከፊ የጥፋት መንገድ መሆኑን ማስተዋል ይገባል::

## 4.2 የመጻሕፍተ ቅዳሴያት አስተምህሮ

የክርስትና እምነት ዐቢይ ምሥጢር የሆነው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ድንግልናዊ ፅንስና ልደት መለኮታዊ ክብሩን በግልጥ ያሳያል፣ የባሕርይ አምላክነቱንም ይመሰክራል፣ ያረጋግጣ ልም:: በመዳን ትምህርት [Soteriology] የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ወሳኝ በመሆኑ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ይህንን መሠረታዊ እምነት አጽንታ ጠብቃ ይዛ ቆይታለች:: ስለሆነም ለዚህ መሠረተ እምነቷ የወላዲተ አምላክ ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና ጉልህ ማስረጃና ምስክር አድርጋ ታስተምራለች::

ለምሳሌ ያህል ብንመለከት ተላውያነ ሐዋርያት (የሐዋርያት ተ ከታዮች) [Apostolic Fathers] ከሚባሉት ቅዱሳን አበው መካከል አንዱ የሆነው ቅዱስ አግናጥዮስ ምጥዉ ለአንበሳ [St. Ignatius of Anotioch (+ A. D 110)] የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና አስመልክቶ ሲናገር «ከቤተ ክርስቲያን ሦስቱ ዐበይት የሥጋዌ ምሥጢራት አንዱ የወላዲተ አምላክ ዘለዓለማዊ ድንግልና ነው» ሲል አስተምሮአል:: በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ



መሠረት ሦስቱ ዐበይት የሥጋዌ ምሥጢራት የሚባሉት «የወላዲተ አምላክ ዘለዓለማዊ ድንግልና፣ በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷና የጌታ ሞት»(286) ናቸው::

በዜና አበው ትምህርት [Patristic Studies] እንደምንረዳው ተላ ውያነ ሐዋርያት የተባሉት ቅዱሳን አበው በተነሡበት ዘመን የተ ዘጋጁት መጠነ ሰፊ ጽሑፎች ወላዲተ አምላክ ማርያም ቅድመ ወሊድ *[ante-portum]*፣ ጊዜ ወሊድ *[in-portum]* ድኅረ ወሊድ *[post-portum]* ወትረ ድንግል ማርያም (ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም) መሆኗን በአጽንኦት ይመሰክራሉ:: ለአብነት ያህል ብንጠቅስ ቅዱስ ሄሬኔዎስ [St. Irenaeus of Lyon] የተባለው አባት ልዑለ ቃል ኢሳይያስ «ሳታምጥ ወለደች፤ ምጥም ሳያገኛት ወልድን ወለደች:: ከቶ እንዲህ ያለ ነገር ማን ሰምቶአል? እንዲህስ ያለ ነገር ማን አይቶአል?» (ኢሳ. 66÷7-8) ብሎ የተናገረውን ቃለ ትንቢት በምሥጢር ተርጉሞ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም መድኅን ክርስቶስን እንበለ ጻዕር፣ እንበለ ሕማም መውለዷን የሚያመለክት ኃይለ ቃል መሆኑን አስገንዝቦአል::(287)

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የትምህርተ ሃይማኖቷ ምሥጢር መድበልና የሥርዓተ አምልኮዋ መዛግብት በሆኑት ቅዳሴያቶቿ ሁሉ ቤዛዊተ ዓለም ማርያም ዘለዓለማዊት ድንግል የመሆኗን ምሥጢር በስፋት ትመሰክራለች:: ይኸውም ከላይ እንደገለጥነው የእመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና ከምሥጢረ ሥጋዌ ዐበይት ምሥጢራት መካከል አንዱና ዋነኛው በመሆኑ ከነገረ ድኅነት ጋር የጠለቀ ግንኙነት አለው::

ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢረ ተዋሕዶ አስመልክቶ የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ ክፍለ ንባብ «... ጸኮት ፍቱሐነ ወግዑዛነ::

(286) Bettenson, *The Early Christian Fathers,* 41. Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept,* 9-11. Carol, *Mariology,* vol., 1 51.

(287) Carol, *Mariology* v. 2, 104-105. Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept,* 21.

ወእምእፋሃ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በ፪ ማርያም ወላዲተ አምላክ ሐዳስ ምእናም፤ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተሰበሰቡት እኒህ ወገኖችህ ከማእሰረ ኃጢአት የተፈቱ፣ ነጻ የወጡ፣ ንጹሐንም ይሁኑ:: ንጽሕት፣ ጽንዕት፣ ክብርት፣ ልዩ በሆነች፤ በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን አምላክን በወለደች በአዲሲቷ መሣሪያ በእመቤታችን አማላጅነት ...»(288) በማለት ይገልጻል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ማርያም አስተምህሮ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሰፊ ድርሻና ከፍተኛ አስተዋጽኦ መሠረት ያደረገ መሆኑን በተደጋጋሚ አውስተናል:: እንደሚታወቀው በምሥጢረ ሥጋዌ አማካይነት በተፈጸመው አምላካዊ የማዳን ሥራ (ሐዲስ ተፈጥሮ) የተገኘው ልዩ ጸጋና ክብር መፍቀሬ ሰብእ የሆነው ቸሩ አምላክ በድቀተ ኃጢአት ለነበረው ዓለም የሰጠው አባታዊ የፍቅር መልስ ነው:: ከዚህም ጋር ይህ አምላካዊ ጸጋና ክብር ኃያሉ አምላክ አስቀድሞ በጥንተ ተፈጥሮ በአርአያውና በመልኩ አክብሮና አልቆ ለፈጠረው የሰው ልጅ ያሰበውና ያዘጋጀው መለኮታዊ ዕቅድ መሆኑን አያሌ የሥነ መለኮት ሊቃውንት አምልተውና አስፍተው ተናግረዋል፣ አስተምረዋል:: በመሆኑም ቀደም ብለን በክፍል 4.1 ሥር የተመለከትናቸውና የእመቤታችንን ዘለዓለማዊ ድንግልና በግልጥ የሚመሰክሩት የተለያዩ ኅብረ አምሳልና ኅብረ ትንቢት የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነትም የሚያስረዱና የሚያረጋግጡ ናቸው:: በዚህም ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በልዕልና የሆነችው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር አስቀድሞ የመረጣትና ያዘጋጃት የድኅነተ ዓለም መሣሪያ መሆኗን ይገነዘቧል::(289)

(288) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 59::

(289) አባ ስብሐት ለአብ፣ «ነግሥ»፣ ገጽ 542:: እስጢፋኖስ ዓምደ ወርቅ (መሪጌታ)፣ "እመቤታችን በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ"፣ *ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣* ገጽ 8:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 3, 100-102.



በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍተ ቅዳሴያት ከርሠ ምሥጢር ውስጥ እንደ ዕንቁ ፈርጥ ዘወትር ሲያበሩ የሚኖሩትና ስለ እመቤታችን ሁለንተናዊ ዜና ሕይወት የሚያወሱት ዘርፈ ብዙ ምሥጢራት አስቀድሞ በዘመነ ብሉይ በተለያየ ኅብረ አምሳል የተገለጡና በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢት የተነገሩ የምሥጢረ ሥጋዌ ጌጦች ናቸው:: በዚህም መሠረት ኦርቶዶክሳዊ የነገረ ማርያም አስተምህሮ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያምን «ማዕረረ ትንቢቶሙ ለነቢያት፤ ፍሬ ወንጌል የተገኘባት የቅዱሳን ነቢያት የተስፋ ትንቢታቸው መከር»(290) በማለት ይገልጻታል:: (ዮሐ. 4÷35-38) ምክንያቱም በዘመነ ሐዲስ የተፈጸሙት የሥጋዌ ምሥጢራት ማለትም የመሲሕ ክርስቶስ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ፣ በኅቱም ድንግልና መወለድ፣ የእረኞች መገረምና መደነቅ፣ የሰብአ ሰገል ከእጅ መንሻ ጋር መምጣት፣ የመድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀቱ፣ ትምህርቱና ተአምራቱ፣ በመጨረሻም ለድኅነተ ዓለም ሲል ራሱን በመስቀል ላይ ቤዛ አድርጎ መስጠቱ፣ መሞቱና መቀበሩ፣ መነሣቱና ማረጉ ሁሉ በዘመነ ብሉይ በተለያየ ኅብረ አምሳልና በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢት የተገጠው ተስፋ ድኅነት ፍጻሜ በመሆኑ ነው:: ይህንን አማናዊ ምሥጢር መሠረት በማድረግ ወርቃማው የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ "ኃስፈ ዝናመ ትንቢት ዘነቢያት ንግበር ለነ መጸወ ዘሐዋርያት»(291)

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ ውስጥ በቅዱሳት መጻሕፍት ምንባባት ጊዜ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት የሚያነበው ሠራዒ ዲያቆን ንባቡን ከመጀመሩ በፊት "ኩሉ ዘኢያፈቅሮ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወዘኢየአምን ልደቶ እማርያም እምቅድስት ድንግል በ፪ኤ ታቦተ መንፈስ ቅዱስ እስከ ምጽአቱ ሐዳስ በከመ ይቤ ጳውሎስ ውጉዘ ለይኩን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወደው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ

(290) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 102. አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 598::

(291) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር፣ ["The Book of Mystery"]* ፣ ገጽ 211::

በድንጋሌ ሥጋ፣ በድንጋሌ ነፍስ፤ አንድም ቅድመ ጸኒስ፣ ድኅረ ጸኒስ፤ ቅድመ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ ድንግል፣ ንጽሕት፣ ክብርት፣ ልዩ ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን የማያምን ቅዱስ ጳውሎስ «ወዘሰ ኢያፈቅሮ ለእግዚእነ ውጉዘ ይኩን እስከ ምጽአቱ ለእግዚእነ እምተስፋ እግዚአብሔር፤ ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን» (1ኛ ቆሮ. 16÷22) እንዳለ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የተለየ ይሁን»(292) እያለ ዘወትር ያውጃል::

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴያት አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በተዋሕዶ ሰው ሆኖ የፈጸመውን አምላካዊ የቸርነት ሥራና አድኅኖት ማዕከል ያደረጉ ናቸው:: በመሆኑም ይህ አምላካዊ የቤዛነት ሥራ በእመቤታችን በኩል በተከናወነው የሥጋዌ ምሥጢር በመፈጸሙ ቅዳሴያቱ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የተዋሕዶ መሠረት፣ የድኅነታችን ምክንያት መሆኗን በስፋት ይገልጻሉ:: ከዚህም ጋር ከእመቤታችን ባሕርይ ተወልዶ ያዳነን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ አማካይነት ፈጽሞ እንደሚዋሐደንና በጸጋውም እንደሚያድነን አስረግጠ ተናግሮአል:: ፍሬ ድኅነት የሚገኝበት ይህ ኀብስተ ሕይወት ወስቴ መድኃኒት (የሕይወት እንጀራና የድኅነት መጠጥ) ከድንግል ማርያም መገኘቱ እመቤታችን በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ጉልህ ድርሻ በግልጥ ያሳያል::(293)

(292) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 75::
(293) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት፣* ገጽ 313:: አባ ስብሐት ለአብ፣ «ነግሥ»፣ ገጽ 542:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia,* 128. ቅዱስ ያሬድ፣ «አንቀጸ ብርሃን» ገጽ 403፣ 408:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ኦርጋኖን፣* ገጽ 158፣ 291:: ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እመቤታችንን ባመሰገነበት ውዳሴው «ትመስሊ ደመና ወትወልዲ ኅብስተ መና ... ትመስሊ መሶበ ... ወታጸግቢ ርኁበ:: ... ትመስሊ ገራህተ ወታፈርዩ ሰዊተ ወታጸድቂ ነፍሳተ ... ወትወልዲ መድኅነ ወትፌውሲ ቍሱላነ ...፤ ረኃብ ነፍስ የጸናበትን ታጠግቢያለሽና መሶብን ትመስያለሽ:: ... የሕይወት እንጀራን ትወልጃለሽና ደመና ትመስያለሽ:: ... ፍሬ ሕይወት የሆነ ጌታን ታስገኚያለሽና እርሻን ትመስያለሽ:: በፍሬ ማኅፀንሽም ነፍሳትን ታድኛለሽ፣ ታጸድቂያለሽ፣ ታከብሪያለሽ:: ... መድኃኒት ክርስቶስን ትወልጃለሽ ድውያንን፣ ሕሙማንን ትፈውሻለሽ:: ...» ሲል ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም የድኅነተ ዓለም መሠረት ለመሆን የበቃችበትን አምላካዊ ጸጋና የተመረጠችበትን ልዩ



በቅዳሴ ጊዜ ከጸሎተ ኪዳን በፊት የሚደርሰው የእመቤታችን ምስጋና «ድኅንነትን የምንለምንሽ ክብርን የተመላሽ ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ:: ሁልጊዜ ድንግል የምትሆኚ (ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ) ድንግል የምትሆኚ አምላክን የወለድሽ የክርስቶስ እናት ሆይ ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ ወደ ልጅሽ ወደ ወዳጅሽ ወደ ላይ ጸሎታችንን አሳርጊ»(294) በማለት እመቤታችን ድኅነተ ሥጋን፣ ድኅነተ ነፍስን የሚሰጠውን አማኑኤል አምላካችንን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና እንደወለደችውና እርሱን በመውለዷም ድንግልናዋ አለመለወጡን ይልቁንም በድንግልናዋ ጸንታ መኖሯን በአጽንኦት ይመሰክራል:: በዚህም እመቤታችን ለአካላዊ ቃል ርደት፣ ለሥጋ ዕርገት መሰላል በመሆኗ ምዕራገ ጸሎት መባሏን ልብ ይሏል::

ይህንን አስመልክቶ ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሲናገር «በከመ ተሠገወ መለኮት በትስብእት ትስብእትኒ ተአምሰለ በመለኮት፤ ረቂቅ መለኮት ግዙፍ ሥጋን በመዋሐዱ ፍጹም ሰው እንደሆነ፤ ግዙፍ ሥጋም ረቂቅ መለኮትን በመዋሐዱ የባሕርይ አምላክ ሆነ»(295) ሲል ገልጾ ተናግሮአል:: በዚህም አማናዊ ምስክርነት ዕርገተ ሥጋ በማኅፀነ ድንግል መፈጸሙን ይገነዘቧል:: በአንጻሩ ደግሞ ይህ ታላቅና ድንቅ ምሥጢር እመቤታችን በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ልዩ ሱታፌ አጉልቶ ያስረዳል::

ከላይ በአጭሩ ከጠቀስናቸው የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ ክፍለ ንባባት በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያናችን ፍሬ ቅዳሴያትም እመቤታችን ወትረ ድንግል ማርያም (ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም) መሆኗን በስፋት ይመሰክራሉ:: ለምሳሌ ያህል ብንመለከት የሠለስቱ ምዕት (የሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ርቱዓነ ሃይማኖት አበው) ቅዳሴ

ክብር ገልጾአል:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ «እሴብሕ ጸጋኪ»፣ *መጽሐፈ ሰዓታት፣* (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም.)፣ ገጽ 212-213::
(294) *መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 81::
(295) አባ ጊዮርጊስ ሳግላዊ፣ [Abba Giyorgis Di Sagla]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር ["Il Libro Del Mistero"] CSCO,* vol. 516. *Scriptores Aethiopici,* 5.

"እግዚአብሔር አብ ዘፈነወ ወልዶ ዋሕዶ ከመ ይኅድር ውስተ ሥጋ ወለተ እንተ ኢተአምር ምተ፤ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር አብ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለውን አንድያ ልጁን ዘርዐ ብእሲን በማታውቅ በእመቤታችን ማኅፀን ያድር ዘንድ ወደዚህ ዓለም ላከው»(296) ይላል:: ይህም ማለት ለወልደ እግዚአብሔር ማደሪያነት የተመረጠውና ለመለኮት ዙፋንነት የተዘጋጀው ማኅፀነ ድንግል ማርያም ዕሩቅ ብእሲ (ፍጡር) ችሎና ደፍሮ የማይቀመጥበት መዝገበ ቃል፣ መንበረ መለኮት፣ መቅደሰ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያስረዳል፣ ያስገነዝባል::

ዳግመኛም የቂሣርያው ሊቅ የቅዱስ ባስልዮስ ቅዳሴ "... ወፈድፋደሰ በእንተ ምልዕተ ምሕረት ኵሎ ጊዜ ቅድስት ወንጽሕት ወላዲተ አምላክ ማርያም ድንግል:: ወትረ ድንግል ማርያም፤ ይልቁንም ሁልጊዜ በረከትንና ቸርነትን በተመላች ጽንዕት፣ ክብርት፣ ልዩ፣ ንጽሕት በምትሆን አምላክን በወለደች፣ መልዕልተ ፍጡራን፣ መትሕተ ፈጣሪ ስለምትሆን ስለ እመቤታችን አማላጅነት ... ቅድመ ጸኒስ፣ ጊዜ ጸኒስ፣ ድኅረ ጸኒስ፤ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ እመቤታችን ዘወትር ድንግል ናት»(297) በማለት የወላዲተ አምላክን ዘለዓለማዊ ድንግልና በግልጥ ይመሰክራል:: በዚህም መሠረት በጉባኤ ቁስጥንጥንያ ካልዕ የተወሰነውንና የተረጋገጠውን "ወትረ ድንግል ማርያም፤ ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም» ወይም በግሪኩ *Aeiparthenos* [Ever-Virgin /Perpetual Virgin] የሚለውን ዐቢይ የነገረ ማርያም አስተምህሮ ምሥጢር መረዳትና መንዘብ ይቻላል::

ከዚህም ጋር የመድኅነ ዓለም ክርስቶስን በድንግልና መፀነስና መወለድ አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በቅዳሴው "ተጸንሰ በከርሥ እንዘ ምሉዕ በኵለሄ፤ ወተወልደ እንዘ ኢያርኁ ማኅተመ ድንግልና፤ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር በምልዓት፣ በጌትነት ሳለ በድንግል ማርያም ማኅፀን ተፀነሰ:: ማኅተመ ድንግልናን ሳይለውጥ ተወለደ»(298) ሲል እመቤታችን

(296) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 294::
(297) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 349::
(298) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 389::



መሲሕ ክርስቶስን በኀቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኀቱም ድንግልና የወለደችበትን ታላቅና ረቂቅ ምሥጢር አድንቋል::

ሌላው ደግሞ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በክብረ ወሊድ ላይ ክብር ድንግልናን በማግኘቷና በመጎናጸፏ አንዳችም ሕማመ ወሊድ ሳያገኛትና ሳይሰማት ወልደ እግዚአብሔርን በኀቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኀቱም ድንግልና የመውለዷን ምሥጢር አስመልክቶ ማኅተመ አበው የተሰኘው ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስ ከዚህ እንደሚከተለው ያብራራል:-

> ... ወካዕበ ንነግር ወንዜኑ ልደቶ እምድንግል ባሕቲቱ ወልዶ አምላክ ዘእምባሕቲታ ወለተ ዳዊት ዘእንበለ አብ ምድራዊ:: ኢሐፃ ፍና ትዕብስት በእንተ ዘአልቦቱ አብ ለዘርዓ ሙላድ:: ... ወበከመ ኢሐፃ ለአዳም እምሕንፃ ሥጋሁ ዘቀዲሙ በእንተ ዘተነቅለ ዓፅመ ገቦሁ:: ከማሁ ኢሐፀ ማኅተመ ድንግልናሃ ለማርያም አመ ወለደቶ ለአበ አዳም በሥጋ:: ወበከመ ኢያሕመሞ ለአዳም ሶበ ተነቅለ ዓፅመ ገቦሁ:: ከማሁ ኢረከባ ሕማመ ወሊድ ለእመ አምላክ ገሊላዊት::(299)

ዳግመኛ ወልደ እግዚአብሔር አባት ሳይኖረው ብቻውን የዳዊት ልጅ ከምትሆን ከድንግል ብቻ መወለዱን እንናገር:: በዘር በሩካቤ ለመወለድ አባት ስላልኖረው የሰውነት ግብር አልጎደለበትም:: ይልቁንም ብቻዋን ድንግል ከምትሆን ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ፍጹም ሰው ሆነ እንጂ:: ... ከጎኑ አንድ አጥንት ስለ ተነሣ አዳምን አካል እንዳልጎደለው፤ አዳምን የፈጠረ ጌታን በሥጋ በወለደችው ጊዜ የእመቤታችን ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም:: ዳግመኛም አዳም ከጎኑ አንድ አጥንት በተነሣ ጊዜ ሕመም እንዳልተሰማው፤ እመቤታችንም ጌታን በወለደችው ጊዜ ሕማም አልተሰማትም::

የዚህ ኃይለ ቃል ምሥጢራዊ ትርጓሜ እመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗንና በዘለዓለማዊ ድንግልናዋ ጸንታ

(299) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 430-431:: *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 162::

መኖሯን ከመግለጡም ባሻገር በቀዳማዊ አዳምና በዳግማዊ አዳም በኢየሱስ ክርስቶስ፣ እንዲሁም በቀዳሚት ሔዋንና በዳግሚት ሔዋን በድንግል ማርያም መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር በግልጥ ያሳያል:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ዳግሚት ሔዋን እመቤታችን በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ ሚና በአጽንኦት ይመሰክራል::

ወርቃማው የቤተ ክርስቲያናችን አባት ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከላይ የገለጥነውንና ቅዱስ ቄርሎስ ስለ እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና የሰጠውን አማናዊ ምስክርነት ከዚህ እንደሚከተለው አጽንቷል፣ አትሟል::

> ወበከመ ሰውዕሰ ዓፅመ ገቦ እምገቦሁ ለአዳም ወኢሐጸ ለአዳም ከማሁ ዓዲ ነሥአ እምድንግል ሥጋ ዘቦቱ ነፍስ ነባቢት ወለባዊት ወኢተወስጠ ድንግልናሃ ኮነ አዳም ፍጹመ እምድኅረ ጸአተ ዓፅመ ገቦ እምኔሁ ወድንግልሂ ዓዲ ነበረት እንበለ ሙስና እምድኅረ ጸአተ ሕፃን እምኔሃ::(300)

ከአዳም ጐን ጐድን አጥንት እንደነሣ አዳም ምንም አካል እንዳልጎደለው፤ እንዲሁ ከድንግል የምትናገር፣ የምታውቅ ነፍስ ያለችው ሥጋን ነሣ፤ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም፤ አዳም የጎድን አጥንት ከእርሱ ከተነሣ በኋላ አካል ሳይጎድለው ፍጹም ሆኖ ኖረ፤ ድንግልም ሕፃን ክርስቶስ ከእርሷ ከተወለደ በኋላ እንዲሁ ያለመለወጥ በድንግልና ጸንታ ኖረች::

በመጨረሻም ገባሬ ተአምራት ወመንክራት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ቀደም ብለን በክፍል 4.1.4 ላይ የገለጥነውን የነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ትንቢታዊ ራእይ መሠረት በማድረግና አማናዊ ምሥጢሩንም በማጽናት «... ወእምቅድስተ ድንግል ወድኅን ተወልደ እግዚእ ተረክበ ፀሐየ ጽድቅ ዘበአማን ሠረቀ፤ ቅድስት ድንግል ከምትሆን ከእመቤታችን መድኃኒት ክርስቶስ ተወለደ:: እውነተኛ ፀሐየ ጽድቅ ጌታ ንዕድ፣

(300) ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ «በእንተ ልደተ እግዚእ» ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 240::



ክብርት ከምትሆን ከምሥራቀ ፀሐይ ድንግል ተገኘ፣ ተወለደ::»(301) በማለት አስተምሮአል:: በዚህም ኦርቶዶክሳዊ ትምህርቱ ለዘለዓለም የማይጠልቀውና ለዓለም ሁሉ የሚያበራው ብርሃነ ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘባት አማናዊት ምሥራቀ ፀሐይ ወላዲተ አምላክ እመቤታችን ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በስዕልና መሆኗን አስገንዝቧል::

በመሆኑም ሰማይ አንድ ፀሐይ ብቻ እንጂ ሌላ ፀሐይን እንዳላስገኘች፤ እንዲሁም አማናዊቷ ዳግሚት ሰማይ እመቤታችንም ፀሐየ ጽድቅ ዘበአማን ከሆነው ከአንድያ ልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ማንንም እንዳላስገኘች (ዕሩቅ ብእሲን እንዳልወለደች) ይመለከቷል:: ይኸውም ይታወቅ ዘንድ መጽሐፍ ከአማናዊት ምሥራቀ ፀሐይ ከድንግል ማርያም የተገኘውን አማናዊውን ብርሃን «ፀሐይ ዘኢየዓርብ:: ወማኅቶት ዘኢይጠፍእ:: ፀሐይ ዘዘልፈ ያበርህ ዲበ ቅዱሳን፤ ኅልፈት፣ ጥፋት የሌለበት፣ የማይጠልቅ ፀሐይ፣ የማይጠፋ ፋና፣ ለዘላለሙ ለቅዱሳን ብርሃን፣ ዕውቀት የሚሆንላቸው ፀሐየ ጽድቅ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»(302) በማለት አስረግጦ ይመሰክራል::

ከዚህም ጋር የነገረ ማርያም መሠረትና የክርስትና እምነት ዐቢይ ምሥጢር የሆነውን የወላዲተ አምላክ ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያናችን የሚዘወተረው የቅዱስ ዲዮስቆሮስ ቅዳሴ «በፈቃደ አቡሁ ወረደ ኀበ ማርያም ተሰንገደ በድንግልናሃ ንጹሕ እግዚአብሔር ተወልደ፤ አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በባሕርይ አባቱ በእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ከልዕልና (ከሰማይ) ወደ ትሕትና (ምድር) መጥቶ ሰው ሆነ:: በማኅፀነ ድንግል ማርያም ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን አደረ:: ንጹሐ ባሕርይ ወልደ እግዚአብሔር ንጹሕ የሚሆን ማኅተመ ድንግልናዋን ሳይለወጥ ተወለደ»(303) ብሏል::

(301) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 456::
(302) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 37::
(303) *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 449::

በምሥጢራዊ ትርጓሜውም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር የእመቤታችንን ማኅተመ ድንግልና ሳይፈታና ሳይለውጥ መወለዱ ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በተዋሕዶ ሰው በሆነ ጊዜ ባሕርየ መለኮቱ አለመወጡን ያጠይቃል:: ይህ ደግሞ በድቀተ ኃጢአት ምክንያት ንጽሐ ጠባዩ አድፎ፣ ቅድስና ባሕርይው ጎድሎ፣ ጸጋው ተገፎ፣ ክብሩም ጎስቁሎ የነበረው መላው የሰው ዘር ወደ ቀደመ ክብሩ ተመልሶ ወደ ጥንተ ርስቱ መግባቱንና የመለኮታዊ ክብር ተካፋይ ለመሆን መብቃቱንም ያረጋግጣል::

**በመምህር አንዱዓለም ዳግማዊ /B.Th. M.A/**
**ሚያዝያ/1998 ዓ.ም.**
**አዲስ አበባ**
andudag@yahoo.com
andudag.dagmawi@utoronto.ca



## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የወላዲተ አምላክ ዘለዓለማዊ ድንግልና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የሚያረጋግጠው እንዴት ነው?
2. በመጀመሪያይቱ ኅትምት (ድንግል) መሬትና በዳግሚት (ሁለተኛይቱ) ኅትምት ምድር በድንግል ማርያም መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ንጽጽር ከነገረ ድኅነት ጋር በማገናዘብ ይግለጹ::
3. በትረ አሮን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም አማናዊት ምሳሌ የሆነችበትን ምክንያት ያብራሩ::
4. የቅድስት ድንግል እመቤታችንን ዘለዓለማዊ ድንግልና በጌዴዎን ፀምር ማስረጃነት በአጭሩ ይግለጹ::
5. ነቢዩ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል የእመቤታችንን ዘለዓለማዊ ድንግልና በተዘጋች ምሥራቃዊት ቤተ መቅደስ ደጃፍ መስሎ የተናገረበትን ምክንያት ከምሥጢረ ድኅነታችን አንጻር ያስረዱ::
6. የወላዲተ አምላክን ዘለዓለማዊ ድንግልና አስመልክቶ ነቢዩ እግዚአብሔር ዳንኤል ያየው ትንቢታዊ ራእይ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለው ምሥጢራዊ ግንኙነት ምንድን ነው?
7. ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም ለአረጋዊው ጻድቅ ለቅዱስ ዮሴፍ እንድትታጭ ያስፈለገው ለምንድን ነው?
8. «የበኩር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም» የሚለውን የማቴዎስ 1፥25 ገጸ ንባብ ያብራሩ::
9. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍተ ቅዳሴያት ስለ ወላዲተ አምላክ ዘለዓለማዊ ድንግልና ያላቸውን አስተምህሮ በአጭሩ ይግለጹ::